ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሰኞ | 84ኛ ዓመት ቁጥር 034 ጥቅምት 4 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# የሰንደቅ ዓላማን ምንነት ለትውልድ በማስረዳት ታሪክን ማስቀጠል ይገባል

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- የሀገርና የሕዝብ ኩራት የሆነውን የሰንደቅ ዓላማ ምንነት ለትውልድ በማስረዳት ታሪክን ማስቀጠል ይገባል ሲሉ አባት አርበኞች ገለጹ።

የጥናታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሰንደቅ ዓላማ ክብር ያለው፣ የሀገርንና የሕዝቡን ማንነት የሚገልጽ ነው።

ጀግኖች አርበኞች በሀገር የሚሰነዘሩ ጥቃቶችን በመከላከል ክብሯን ለማስጠበቅ በጦርነት በሚወድቁበት ወቅት አንደኛውና ዋናው ምልክታቸው ሰንደቅ ዓላማ መሆኑን አስታውቀዋል።

ለወጣቶች ዋጋ ስለተከፈለበት የሰንደ ቅዓላማ ምንነት፣ ማንነት፣ በዓሉ እንዴት መከበር እንዳለበት እንዲሁም ስለሀገራችን ባህል፣ ታሪክና ዕምነት ከትምህርት ቤት ጀምሮ ማሳወቅ ከተቻለ የሰንደቅ ዓላማ ክብር ይበልጥ ይገለጣል ብለዋል።

የሰንደቅ ዓላማ ቀንን ማክበር ታላቅነትና ለሀገሪቱ ክብር የሚገባ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ቀደም ባሉት ጊዜያት የዓድዋ፣ የማይጨው እና ሌሎች ጦርነቶች ሲካሄዱ ሰንደቅ ዓላማ ተይዞ ነው። ድል ሲደረግም ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ብሎ ይውለበለባል ሲሉ ተናግረዋል።

ሰንደቅ ዓላማ የሚከበርበት ዋናው ምክንያት አባትና እናቶቻችን ሰንደቅ ዓላማ ሀገራችንና ሕዝባችንን ይወክላል በሚል ዋጋ ስለከፈሉበት፣ ደማቸውን ስላፈሰሱበት፣

የሰንደቅ ዓላማን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# የኢትዮጵያ እድገት ሌላኛው አቅም

**ዳግማዊት አበበ**

**ዜና ትንታኔ**

ኢትዮጵያ 70 በመቶ የሚሆነውን የማዕድን ሀብቷን እስካሁን ማወቅ አለመቻሏን ጥናቶች ያመለክታሉ። ለዚህም የሥነ-ምድር መረጃዎች አለመገኘትና ፍሊጋው ባህላዊ መንገዶችን ተከትሎ መካሄድ ምክንያት መሆኑ ይነገራል።

የኢትዮጵያ እድገት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ሩዝ- ለኢኮኖሚ ሉዓላዊነት ሌላኛው አማራጭ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



በኢትዮጵያ አምስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ለሩዝ ምርት ተስማሚ የሚሆን መሬት እንዳለ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

እ.ኤ.አ በ2020 በኢትዮጵያ ግብርና ኢንስቲትዩት የፎገራ ብሔራዊ የሩዝ ምርምርና ሥልጠና ማዕከል ‹‹የሩዝ ምርታማነት፣ ግብ፣ አቅምና ተጽዕኖ በኢትዮጵያ›› በሚል ርዕስ ያስጠናው ጥናት እንደሚያመለክተው፤ ሶስት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ተጨማሪ በመስኖ የማልማት አቅም አለ። ጥናቱ ይህንን ቢልም ሀገሪቷ አሁንም በየዓመቱ ለሩዝ ግዢ የሚውል በርካታ የውጭ ምንዛሬ ታወጣለች።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያመለክተው ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ ከ2020 እስከ ሜይ 2023 ብቻ አንድ ሚሊዮን 421 ሺህ 517 ነጥብ 55 ቶን ሩዝ ከውጭ ተገዝቶ 37 ቢሊዮን 473 ሚሊዮን 196 ሺህ 538 ብር ወጪ ተደርጓል። ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደሀገር በሩዝ ዘርፍ የተጀመረው አበረታች እንቅስቃሴ ለችግሩ መፍትሔ ያዘለ ይመስላል።

ባለፉት ዓመታት በተሠራው ሥራ የሩዝ ምርት የመሬት ሽፋንን ከ180 ሺህ ሄክታር ወደ አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ማሳደግ መቻሉን ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

ቀደም ሲል ሩዝ በአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር አካባቢ፣ በኦሮሚያ ክልል እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ጉራፈርዳ አካባቢ ብቻ ይመረት የነበረ ቢሆንም አሁን ላይ በኢኒሼቲቭ በሁሉም ክልሎች እየተመረተ ስለመሆኑም የሚኒስቴሩ መረጃዎች ያሳያሉ።

በተለይ ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሬቶች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ መረጃው የሚጠቁም ሲሆን በ2030 ከውጭ የሚገባውን የሩዝ ምርትን ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ለመተካት እቅድ መያዙ ተገልጿል።

ከሶስትና አራት ዓመታት ወዲህ የጀመረችው የሩስ እርሻ የማስፋፋት ሥራም የሀገሪቱ ምግብ ዋስትና

ሩዝ- ለኢኮኖሚ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





አቶ ዘማች ክፍሌ

## በጌዴኦ ዞን ትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ፡-

- 122 አዳዲስ መማሪያ ክፍሎች ተገንብተዋል
- 574 መማሪያ ክፍሎች ተጠግነዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ዲላ፡- ባለፉት ሶስት ወራት በጌዴኦ ዞን ”ትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ ከ32 ሚሊዮን ብር በላይ እንደተሰበሰበ፤ 122 አዳዲስ መማሪያ ክፍሎች ተገንብተው ለአገልግሎት መብቃታቸውን እና 574 መማሪያ ክፍሎች መጠገናቸውን የዞኑ ትምህርት መምሪያ አስታወቀ።

የጌዴኦ ዞን ትምህርት መምሪያ ኃላፊ አቶ ዘማች ክፍሌ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጪነት የተጀመረው የትምህርት ቤቶች ደረጃን የማሻሻል “ትምህርት ለትውልድ” ንቅናቄ ሥራ በዞኑ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል።

በንቅናቄው ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ባለሀብቶች፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲሁም የተለያዩ ግለሰቦች እየተሳተፉ መሆኑን የገለጹት አቶ ዘማች፤ ባለፉት ሶስት ወራት በጌዲዮ ዞን “ትምህርት ለትውልድ” ንቅናቄ ከ32 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን ገልጸዋል።

ባለፉት ሶስት ወራት 122 አዳዲስ መማሪያ ክፍሎች ተገንብተው ለአገልግሎት መብቃታቸውን ገልጸው 574 መማሪያ ክፍሎች እንደተጠገኑ ተናግረዋል። ባለፈው ዓመት ከ73 ሚሊዮን ብር በላይ የተሰበሰበ ሲሆን በዚህም 202 አዲስ መማሪያ ክፍሎች እንደተገነቡ እና 627 መማሪያ ክፍሎች እንዲሁም ከአራት ሺህ በላይ የተማሪዎች መቀመጫና ጥቁር ሰሌዳዎች እንደተጠገኑ ተናግረዋል።

በ2015ዓ.ም በጌዲዮ ዞን ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 94 በመቶ የሚሆኑት ከደረጃ በታች እንደነበሩ የገለጹት አቶ ዘማች ክፍሌ፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት በተሠራው ሥራ 12 በመቶ የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹና ደረጃቸውን እንዲጠብቁ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

አሁን ላይ በዞኑ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 88 በመቶ የሚሆኑት ከደረጃ በታች እንደሆኑ የተናገሩት አቶ ዘማች ክፍሌ፤ ተማሪዎች በእውቀት፣ በአመለካከት እና በክህሎት ታንጸው እንዲወጡ የትምህርት ቤት መሠረተ ልማት ማሟላት አስፈላጊ በመሆኑ ህብረተሰቡ የጀመረውን ተሳትፎ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

# ኢትዮጵያ ከራሷ ባሻገር ለጎረቤቶቿ የሎጂስቲክስ ማዕከል እንድትሆን እየተሠራ ይገኛል

- አቶ አህመድ ሽዴ
የገንዘብ ሚኒስትር

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- «ኢትዮጵያ ከራሷ ባሻገር ለጎረቤቶቿ የሎጂስቲክስ ማዕከል እንድትሆን መንግሥት በቁጠኝነት እየሠራ ይገኛል» ሲሉ የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ ገለጹ።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ በሎጂስቲክስ ዘርፍ የላቀ አፈጻጸም ላስመዘገቡ አካላት በተዘጋጀው የእውቅና መድረክ ላይ ተገኝተው እንደተናገሩት፤ መንግሥት በሎጂስቲክስ ዘርፍ ሰፊ ኢንቨስትመንት እያከናወነ ሲሆን ከጎረቤት ሀገራት ጋር በትብብር እየሠራ ይገኛል፡፡

ለአብነትም ከኬንያ እንዲሁም በቅርቡ ከደቡብ ሱዳን ጋር በሎጀስቲክስ ዘርፍ ለመስራት ስምምነት መደረጉን ገልጸው፤ ይህም አትዮጵያ ከራሷ ባሻገር ለጎረቤቶቿ የሎጂስቲክስ ማዕከል ሆና እንድትወጣ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ሎጂስቲክስ ሥርዓቱን ለማሻሻል በቻይና መንግሥት ድጋፍ ከጅቡቲ ጋር የተደረገው በባቡር ኢንቨስትመንት በአሁኑ ጊዜ ጥሩ ውጤት እያመጣ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በሎጂስቲክስ ዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድትሆን በዋነኝነት በሪፎርሙ ትኩረት የተሰጠው መሆኑን አውስተው፤ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በዘርፉ በተለያዩ ሴክተሮች እንዳይሳተፉ ማነቆ የነበሩ የተለያዩ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የሪፎርም ሥራዎች ሲሠሩ ቆይቷል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዘርፉ ላይ በስፋት ኢንቨስት በማድረግ በተለይ በካርጎ ሎጂስቲክስ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን ጠንካራ ሥራ እየሠራ መሆኑን ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

መንግሥት የአየር መንገዱን አቅም ለማሳደግና አዲስ ኤርፖርት ጭምር ለመገንባት ሥራዎች እየተሠሩ ነው።ለአብነትም አየር መንገዱ የጭነት አገልግሎትን የበለጠ ቀልጣፋ ለማድረግና የሀገሪቱን የገቢና የወጪ ንግድ እንቅስቃሴ ለማሳደግ እየገነባ የሚገኘው የካርጎ ተርሚናል ማስፋፊያ ሥራ ጥሩ አፈጻጸም ላይ የደረሰ ሲሆን ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።


ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሙ ሎጂስቲክስ እንዲሻሻል ዓላማ አድርጎ ማስቀመጡን ጠቅሰው በዚህም ጥሩ ውጤት እየተመዘገበ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በርካታ ሕዝብ ያላት፤ ኢኮኖሚዋም እያደገ መምጣቱን የጠቆሙት አቶ አህመድ፤ የማሪታይም ሎጅክስቲክስ ሥራዎች ወሳኝ ናቸው ብለዋል።በዘርፉ የተመዘገቡ ውጤቶች በሀገር ኢኮኖሚው እድገት ላይ ትልቅ ሚና እየተጫወተ መሆኑንም አመላክተዋል።

በተለይም የዘርፉን አሠራሮችን በማዘመን፣ መሠረተ ልማት ማሟላት፣ ብቁ የሰው ሃይል ማፍራትና ኤክስፖርት ሎጂስቲክስን ከማስፋት አንጻር በተከናወኑ ተግባራት ውጤቶች መመዝገባቸውን አመላክተዋል።

# የመልሶ ግንባታው ሌላኛው ገፅ

**ቃልኪዳን አሳዬ**



ግጭት በዜጎች ላይ ጥሎ ከሚያልፋቸው አያሌ ጠባሳዎች መካከል አንዱ የሥነ ልቦና ቀውስ ነው።ግጭት በሰው ሕይወት እና በንብረት ላይ ከሚያደርሰው ውድመት ባለፈ የዜጎችን የረጅም ጊዜ ማህበራዊ መስተጋብር እና የሥነልቦና ደህንነት የማዳከሙ ጉዳይ የአደባባይ እውነታ ነው።

በሀገራችን በተከሰቱ ግጭቶች በርካታ ዜጎች የሥነልቦና ቀውስ እንዳጋጠማቸው ይነሳል።ተጎጂዎች ከሚፈጠርባችው የማህበራዊ ሥነልቦና ጉዳት ለማገገም በተናጠል ወይም በጋራ የሚደረግ የሥነልቦና ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸውም በባለሙያዎች ይነገራል።

የሥነ ልቦና ህክምና ባለሙያዋ ትግስት ዋልተንጉሥ፤ ከግጭት በኋላ ትኩረት የሚሰጠው ለምግብ፣ አልባሳትና ቁሳቁስ ነው።ነገር ግን ግጭቱ በዜጎች ላይ ጥሎት ያለፈው የሥነልቦና ጠባሳ ይዘነጋል ይላሉ።

ከግጭት ጋር የተያያዙ ጉዳቶችን በአእምሯዊ ጤና እና በሥነ ልቦና ድጋፍ መርሃ ግብር አማካኝነት ወደትግራይ ክልል በመጓዝ የሥነልቦና ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች ድጋፍ ማድረጋቸውን የሚጠቅሱት ባለሙያዋ፤ በወቅቱ ዜጎች ወደቀደመው ሕይወታቸው ለመመለስ ጥረት እያደረጉ ቢሆንም እንኳን የሥነልቦና ችግር ትልቅ እንቅፋት እንደሆነባቸው መመልከት መቻላቸውን ይገልፃሉ።

እንቅልፍ ማጣት፣ የበቀል ስሜት፣ ድባቴ፣ ጭንቀት፣ ተስፋ ማጣትና ሌሎች አላስፈላጊ ስሜቶች እንደሚስተዋልባቸው አመላክተው፣ እነኚህ ስሜቶች ካልታከሙ ከዜጎቹ ጋር አብሮ የመቆየት እድላቸው ሰፊ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

ወይዘሮ ትግስት በዚሁ ፕሮግራም አማካኝት ከትግራይ በተጨማሪ በአፋርና አማራ ክልሎች ተንቀሳቅሰው ሠርተዋል።በሁለቱ ክልሎች ዜጎች በማህበር፣ እድር፣ እቁብና በሌሎችም ማህበራዊ መስተጋብሮች ተሳስረው ረጅም ዓመታትን ቢያሳልፉም፣ ከግጭቱ በኋላ እነኚህን መስተጋብሮች እያቆሙ እንደሆነና እንዲሁም ከትዳር አጋሮቻቸውም ጋር ግንኙነት ማድረግን ያቋረጡ መኖራቸውን እንደተረዱ ይገልፃሉ፡፡

እንደ ባለሙያዋ ማብራሪያ፤ የበቀልና መከፋት ስሜቶች መታከም አለባቸው፤ ይህ የማይሆን ከሆነ ዜጎች ተመልሰው ወደግጭት መግባታቸው የማይቀር ነው።የፈረሰ ትምህርት ቤት፣ መንገድ፣ የእምነት ተቋማትና ሌሎችም ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ብቻ ሳይሆኑ የዜጎች ስሜትም መታደስ አለበት።ይህ የማይሆን ከሆነ ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፍ ጠባሳ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

ግጭቱ በዜጎች ላይ ያስከተለውን የአዕምሮ ቁስል ጠባሳ (Trauma) ለማጥፋት እንደሀገር ፕሮግራም ያስፈልጋል፤ ሥለሥነልቦና ጤና ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የሃይማኖት አባቶችና ሌላውም ዜጋ ሊያውቅ ይገባል።ችግሩን ለመፍታትም መንግሥትን ጨምሮ የእምነት ተቋማት፣ እድሮችና ሌሎችም ማህበራዊ ተቋማት በጋራ ሊሠሩበት ይገባል ሲሉ ባለሙያዋ ያስገነዝባሉ፡፡

በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የቀዶ ጥገና ባለሙያውና የህቂ ፋውንዴሽን ሃላፊ ዶክተር ፋሲካ አምደሥላሴ በበኩላቸው እንደሚገልጹት፤ ድህነት ባለበት ሀገር ግጭት በመስፋፋቱ ዜጎች ለችግር መዳረጋቸው በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኗል።ግጭቱ ከቁሳዊና አካላዊ ጉዳት በተጨማሪ በዜጎች ላይ ከፍተኛ የሥነ ልቦና ቀውስ እንዲገጥም ያደረገ ሲሆን፤ በዚህም ሞት፣ ረሃብ፣ ጉስቁልናና የተለያዩ በሽታዎች በየዜጎች ቤት ደርሰዋል፡፡

ጦርነት ከሚያመጣቸው ጉዳቶች አንደኛውና ዋነኛው የሥነልቦና ቀውስ ሲሆን ይህም በትግራይ ክልል በስፋት እየተስተዋለ ይገኛል የሚሉት ዶክተር ፋሲካ፤ ከእርስ በእርስ ግጭቱ በኋላ በመምህራንና በጤና ባለሙያዎች ላይ ብቻ በተደረገ ጥናት እስከ 90 በመቶ በሚደርሱ ዜጎች ላይ ጭንቀት፣ ፍርሀት፣ ተስፋ መቁረጥና ሌሎች ተመሳሳይ የሥነ ልቦና ቀውሶች እንደተጋረጠባቸው ይጠቁማሉ፡፡

ዶክተር ፋሲካ እንደሚናገሩት፤ በኢትዮጵያም ሆነ በክልሉ ያሉ የሥነልቦና ባለሙያዎች ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ እያንዳንዱን ዜጋ ለማከም አስቸጋሪ ነው።ለዚህም በትንሽ ባለሙያ በርካታ ዜጎች ጋር መድረስ የሚቻልበትን አዲስ የፈጠራ ሃሳብ በማመንጨት ችግሩን ለመቀነስ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

የነጻ ስልክ መስመር በማቋቋም ዜጎች ለሥነልቦና ባለሙያዎች እየደወሉ ችግሮቻቸውን እንዲያማክሩ በማድረግ እንዲሁም በትምህርት ቤቶችና በጤና ተቋማትም ተማሪዎችና ታካሚዎችን በማሠልጠን ስለሥነልቦና ጤና የሚሰጠው ትኩረት እንዲያድግ ጥረቶች እየተደረጉ መሆናቸውን ዶክተሩ ይናገራሉ፡፡

የሥነልቦና ችግር በምርታማነት ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያደርስ በመሆኑ የሚመለከታቸው አካካላት ሊረባረቡ እንደሚገባ የሚናገሩት ዶክተር ፋሲካ፤ በሚዲያዎች ላይ የሥነ ልቦና ህክምና ባለሙያዎች ስለአዕምሮ ጤና ጉዳዮች በደንብ ሃሳብ እንዲሰጡ ማድረግና ተከታታይ የቴሌቪዥንና ራዲዮ ድራማዎችን በማሰራጨት ከዚህ ቀደም ልክ ኤች አይቪ ላይ በስፋት በመስራት መቀነስ እንደተቻለው ሁሉ በሥነልቦና ጤናም ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት አለበት ሲሉ ይመክራሉ፡፡

# “በአዲስ አበባ የተሠሩ የልማት ሥራዎች የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷን የሚመጥኑ ናቸው”


## - አፍሪካውያን ጎብኚዎች

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ የኮሪደር ልማቱን ጨምሮ የተሠሩ የተለያዩ የልማት ሥራዎች መዲናዋን እና የአፍሪካ ህብረትና የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ መቀመጫነቷን የሚመጥኑ መሆናቸውን አፍሪካውያን ጎብኚዎች ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ርዕሰ መዲና እና የአፍሪካ ዲፕሎማሲያዊ ማዕከል የሆነችው አዲስ አበባ የመሠረተ ልማት አውታሯን ለመለወጥ አቅዳ እየሠራች ያለው የልማት ሥራ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ መቀመጫነቷን በትክክል የሚመጥኑ መሆናቸውን የሴኔጋልና ኬንያ ጎብኚዎች ገለጹ።የመንገድ ደረጃዎችና የመንገድ ዳር ልማቶች ለከተማዋ ውበት የሰጡ መሆናቸውንና ይህም ወጥና ደረጃውን የጠበቀ ከተማ እንዳደረጋት ተናግረዋል፡፡

6ኛውን የሚላን የከተማ የምግብ ፖሊሲ ስምምነት ፎረም ለመካፈል አዲስ አበባ የተገኘው ሴኔጋላዊው ጆሴፍ ሳምቡ፤ አዲስ አበባ ጉልህ የልማት ፕሮጀክቶችን በማከናወን ላይ መሆኗን እንደታዘበ ተናግሯል።የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ እና የበርካታ ዲፕሎማሲያዊ ተልእኮዎች ማዕከል የሆነችው አዲስ አበባ ዘመናዊ የከተማ ገጽታ በመፍጠር የመንገድ እና የኮሪደር ልማቶች አስደናቂ ስኬቶች ጎልተው ማየታቸውን ጠቅሷል። ይህም ከተማዋ የአፍሪካ


ጆሴፍ ሳምቡ


ኤሪክ ኦጋሉ

ህብረት መቀመጫነቷን በትክክል የሚመጥን እንደሆነ ጠቁሟል፡፡

የከተሞች መሻሻል ለአንድ ሀገር ወሳኝነት ያለው መሆኑንና ለዚህ ደግሞ የልማት ፕሮጀክቶች ቀዳሚ መሆናቸውን ገልጿል።በአዲስ አበባ የታየው ተግባርም ይህንን ያስመለከተ እንደሆነ ተዘዋውሮ ከተመለከተው ትዝብቱ ተናግሯል።

ኬንያዊው ኤሪክ ኦጋሎ በበኩሉ፤ ምንም እንኳን አዲስ አበባን ለመጀመሪያ ጊዜ ቢያያትም በተለያየ አጋጣሚ ከሚያገኘው መረጃ አንጻር ከተማዋ ታሪካዊ መሆኗን ይናገራል።አሁን ላይም ከተማዋ ፈጣን እድገት ላይ መሆኗን መገንዘቡን ገልጿል፡፡

የአዲስ አበባ የማስዋብ ሥራ አድናቆት የሚሰጠው ነው ያለው ኤሪክ፤ ጎዳናዎች እና መንገዶች በከፍተኛ ደረጃ መለወጣቸውን፤ ይህም ከተማዋን በከተማ ፕላን የአህጉሪቱ ተምሳሌት የመሆን ምኞቷን የሚያመለክት ወጥ የሆነ መልክ እንዲይዝ ማድረጉን ተናግሯል።

የመንገድ ሥራ ወጥነት እና መሻሻሉ የአዲስ አበባን ውበት እንዳሳደገው፤ ከተማዋ በፍጥነት እየተቀየረችና ዘመናዊነትን እያስቀጠለች መሆኗን፤ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የከተማ ከባቢ ለመፍጠር ከሚተገበረው ራዕይ ጋር የሚስማማ እንደሆነ አመላክቷል፡፡

በአጠቃላይ አዲስ አበባ እያከናወነች ያለው የልማት ሥራ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫነቷን ብሎም የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷን የሚመጥን ነው ያለው ኤሪክ፤ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራትም ከዚህ ልምድ በመነሳት በከተማ የልማት ሥራዎች ላይ ጥራትንና ወጥነትን ለማስጠበቅ ትምህርት የሚያገኙበት መሆኑንም ጠቅሷል፡፡

# ግብፅ በዓባይ ወንዝ ላይ የምታራምደው የ “እኔ ብቻ ልጠቀም” እሳቤ ጊዜው አልፎበታል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ግብፅ የምታራምደውን የእኔ ብቻ የሚል ያለፈበት እሳቤ ትታ ከዓባይ ተፋሰስ ሀገራት ጋር በትብብር መሥራት እንደሚገባት በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሰርቬይንግና ካርታ ኢንጅነሪንግ መምህር ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን ኤርዱኖ ገለጹ፡፡

ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ዓመታት የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት የትብብር ማእቀፍ ባለመኖሩ አንዱ አንዱን ለማጥፋት በሚደረግ የፖለቲካ ድራማ ላይ የተመሠረተ አካሄድ ይስተዋል ነበር፡፡ የትብብር ማእቀፉ መኖሩ አንዱ ሀገር ሌላኛውን ሀገር ሳይበድል የውሃ ዋስትናው የሚከበርበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ግብፅም የምታራምደውን የእኔ ብቻ የሚል ያለፈበት እሳቤ ትታ ከተፋሰሱ ሀገራት ጋር በትብብር መሥራት ይኖርባታል ብለዋል፡፡

ሁሉም የተፋሰሱ አባል ሀገራት በባለሙያ የተደገፈ ትንተና ተካሂዶ የየሀገራቱ ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ ታውቆና በጋራ የሚጠቀሙበትን መንገድ መፈለግ እንደሚገባ ጠቁመው፤ ይህም በርካታ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ አንዱ ሀገር በሌላው ላይ ችግር እየፈጠረ አለመረጋጋትና ሰላም ማጣት እንዲፈጠር የሚያደርግበት ሁኔታ እንደሚቀርም ገልጸዋል፡፡

ግብፅ በዓለም ከሚታወቀው ከፍተኛ የከርሰ ምድር ውሃ ካላቸው ሀገራት አንዷ ናት ያሉት ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን፤ ከዚህም በተጨማሪ ሁለት ባህርና ሲዊዝ ካናልም አላት፡፡ ሀገሪቱ ከግማሽ በላይ በውሃ የተከበበች ናት ብለዋል፡፡

ይህ ሁሉ የውሃ ሀብት እያላት ዓባይ ጥገኛ ነኝ ብላ መቶ በመቶ ለእኔ ነው የሚገባው የሚለው ስግብግብነት የትም እንደማያደርስ ጠቅሰው፤ የሌሎች ሀገሮች ሕዝብ እያደገ በሄደ ቁጥር በዓባይ ወንዝ የመጠቀም ፍላጎት እጨመረ እንደሚሄድ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይህን አጀንዳ ማቆምና በምን መልኩ በትብብር መጠቀም እንደሚቻል ማሰብ መቻል አለባት ብለዋል፡፡

እንደ ምሁሩ ገለጻ፤ የግብጽ ያረጀ እሳቤ የሚያበቃበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም፡፡ ሀገራት ሕዝባቸው በጨመረ


ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን ኤርዱኖ

ቁጥር ያላቸውን ሀብት ወደመጠቀም ይመጣሉ፡፡ ግብጽ በዚህ ግትር አቋሟ የምትቀጥል ከሆነ ከተፋሱ ሀገራት የሚገጥማት ተቃውሞ እየጨመረ ይመጣል፡፡

ኢትዮጵያ ከዓባይ ውሃ 86 በመቶ የሚሆነውን እንደምታበረክት አስታውሰው፤ የውሃው ዋንኛ ተጠቃሚ ሆና የቆየችው ግብፅ ኢትዮጵያን እንደጠላት መቁጠሯ ግርምት የሚፈጥር ነው፡፡ ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት የመጠቀም መብት አላት ብለዋል፡፡

የተፈጥሮ ሀብቷን ለምን ተጠቀመች ተብሎ የሚመጣባትን ጠላት ለመመከት መላው ኢትዮጵያውያን በአንድነትና በትብብር መመከት ይኖርባቸዋልም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ግብፅ ዛሬ ኢትዮጵያ ላይ የምታደርሰው ጫና የሚሳካላት ከሆነ ነገ ወደ ሌሎችም የተፋሰሱ ሀገራት መዞሯ እንደማይቀር ገልጸው፤ ሁሉም የተፋሰሱ ሀገራት ለፍትሐዊ ተጠቃሚነት መሥራና ከኢትዮጵያ ጎን መቆም እንዳለባቸውም አመላክተዋል፡፡

# ኢትዮጵያውያን ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው ሰርተፍኬት በሚያስገኘው የ“ኮደሮች” ሥልጠና ሊሳተፉ ይገባል

## - ከ242 ሺህ በላይ ሠልጣኞች የኮደሮች ሥልጠናን እየተከታተሉ ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን ዓለም አቀፍ እውቅናና ተቀባይነት ያለው ሰርተፍኬት በሚያስገኘው የ”ኮደሮች” ሥልጠና ሊሳተፉ እንደሚገባ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ፡፡ የአምስት ሚሊዮን “ኮደሮች” ይፋ ከተደረገ ጀምሮ ላለፉት ሶስት ወራት ከ242 ሺህ በላይ ሠልጣኞች ተመዝግበው ትምህርታቸውን እየተከታተሉ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ እንደገለጹት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ያስጀመሩት የአምስት ሚሊዮን “ኮደሮች” ሥልጠና በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና እና ተቀባይነት ያለው ሰርተፍኬት የሚሰጥበት ነው፡፡

በመሆኑም ታዳጊዎች፣ ወጣቶች፣ የመንግሥት ሠራተኞች እና በተለያየ የሥራ መስክ ውስጥ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች የእድሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል ብለዋል፡፡

የአምስት ሚሊዮን “ኮደሮች” ሥልጠናን በተመለከተ የተለያዩ አካላት ጥያቄ እያቀረቡ መሆኑን ገልጸው፤ ሥልጠናው ምንም ዓይነት ክፍያ የማይጠየቅበት ነው፡፡ የመመዝገቢያ ሊንኩም በመንግሥት ኮሙኒኬሽን ይፋዊ ገጽ ላይ በተለያየ ጊዜ እያሳወቅን ነው ሲሉ አስታውቀዋል፡፡

ሠልጣኞች በኦንላይን በነጻ ተመዝግበው ሥልጠናውን በማንኛውም ቦታ ሆነው በስልካቸው መከታተል ከመቻላቸውም በተጨማሪ ለሥልጠና በተዘጋጁ የትምህርት ተቋማት መከታተል እንደሚችሉ ተናግረዋል፡፡

ሥልጠናው የኢትዮጵያ ወጣቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፈላጊ የሆኑ የዲጂታል ክህሎት እንዲኖራቸው ለማድረግ የተቀረጸ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የአምስት ሚሊዮን “ኮደሮች” ይፋ ከተደረገ ጀምሮ ላለፉት ሶስት ወራት ከ242 ሺህ በላይ ሠልጣኞች ተመዝግበው ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉና ያጠናቀቁ ሠልጣኞች መኖራቸውን አስረድተዋል፡፡


ሰላማዊት ካሳ

ለሥልጠናው በአጠቃላይ ከተመዘገቡት ሠልጣኞች ውስጥ ከ81 ሺህ በላይ የሚሆኑት መሠረታዊ የፕሮግራሚንግ ሥልጠና፣ ከ78 ሺህ በላይ የሚሆኑት ደግሞ መሠረታዊ የዳታ አናላይስስ ሥልጠና እየተከታተሉ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

ከ82 ሺህ በላይ የሚሆኑት ደግሞ መሠረታዊ የአንዲሮይድ አፕሊኬሽን ላይ እየተሰጠ ያለውን ሥልጠና እየወሰዱ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

# የኢትዮጵያ እድገት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የኢትዮጵያ የማዕድን ሀብት ፍለጋና ጥናት ጉዞ ደካማ መሆን እንዲሁም ፍለጋው በቴክኖሎጂ የተደገፈ አለመሆን ሀገሪቱ ካላት የማዕድን ሀብት ከ30 እስከ 40 በመቶ የሚሆነው ብቻ ማወቅ እንድትችል ያደረጋት ሲሆን ይህም ያላትን ማዕድን ሀብት ባግባቡ እንዳትጠቀም የሚያደርጋት ምክንያት እንደሆነ ይነሳል።

ለመሆኑ ኢትዮጵያ ካላት ማዕድን አንጻር ምን ያህል እየተጠቀመች ነው? በዚህ ዘርፍ ያለው ሕገወጥነት ምን ይመስላል? እንዴትስ መከላከል ይቻላል? የሚሉ ጉዳዮች ላይ የዘርፉ ምሁራንና ሃላፊዎች ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የማይኒንግ መምህር ኤሊያስ ካሳሁን ፤ በሀገራችን ያለው የማዕድን ሀብት በየቦታው ተበታትኖ ያለ ነው። ይህም ጠለቅ ያሉ የአሰሳ ጥናቶች እንዳይካሄዱ ያደርጋል ይላሉ።

በኢትዮጵያ ብዙ የማዕድን ክምችት ያሉባቸው ቦታዎች አሁን ላይ ግጭቶች አሉባቸው ያሉት መምህሩ ለአብነትም ትግራይ፣ ወለጋ እንዲሁም ጉጂ ማንሳት ይቻላል። በነዚህ አካባቢዎች ግጭቶች ባይኖሩ ጥሩ የማዕድን ሀብት ያሉባቸው ነበሩ ሲሉ ይገልጻሉ።

በግጭትና በተለያዩ ምክንያቶች ነባር የሆነው በጉጂ ዞን የሚገኘው የሚድሮክ ወርቅ ማምረቻ ድርጅት ባሁኑ ጊዜ በዓመት እስከ 3 ነጥብ 5 ቶን እያመረተ ይገኛል ያሉት አቶ ኤልያስ ቀደም ባሉ ዓመታት ግን እስከ 8 ቶን ይመረት ነበር ይላሉ።

ሌላው ዘርፉን እየጎዳ ያለው ሕገወጥነት መሆኑን የሚያነሱት መምህሩ ይህም ማዕድን አውጪዎችን የሚጎዳና ጥራት ያለው የማዕድን ምርት እንዳይገኝ የሚያደርግ ሲሆን በተለይም በቤኒሻንጉልና በጋምቤላ ክልሎች በርካታ የወርቅ ማዕድን ቢኖርም በግለሰቦች በሕገወጥ መንገድ ተይዞ እንደሚገኝ ይናገራሉ።

በዓለም ላይ ማዕድን በባህላዊ መንገድ እንዲወጣ የፈቀደች ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት። ይህም ያለውን የማዕድን ሀብት በዘላቂነት እንዳንጠቀም ያደርጋል ሲሉ ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያ ካላት የማዕድን ሀብት 3 በመቶ የሆነውን



እንኳን አልተጠቀመችም ያሉት አቶ ኤልያስ፤ ያለውን ሀብት መጠቀም ብቻም ሳይሆን ማዕድናቱ ያሉበት ቦታዎችን መለየት በራሱ ትልቅ ሥራ የመሚጠይቅ ነው ይላሉ።

አቶ ኤልያስ፤ አሁን ላይ ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ሀብት በአግባቡ እንድትጠቀምና በዘርፉ ያሉ ሕገወጥነትን ለመከላከል አዲስ ተግባራዊ የተደረገው የገንዘብ ፖሊሲ ማሻሻያው እያገዘው እንደሚገኝ አንስተው ዘርፉ ከፍ ያለ የፋይናንስ ወጪ የሚጠይቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት ጠለቅ ያሉ ጥናቶችን ማካሄድ እንደሚኖርበት ይጠቁማሉ።

የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ከከበሩ ማዕድናት እስከ ግንባታ በርካታ ማዕድናት ያላት ሀገር ናት። መንግሥትም ባለፉት አምስት ዓመታት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት ዘርፉን ከአምስቱ የኢኮኖሚ ምሰሶዎች አንዱ በማድረግ በማልማት ላይ መሆኑን ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ ከማዕድን ዘርፉ ማግኘት ያለባትን ጥቅም አላገኘችም የሚሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይህም የሆነው ለበርካታ ዓመታት ለዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶ ባለመሠራቱ ነው ይላሉ።

ሌላው በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት ከወርቅ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ሕገወጥነት አጋጥሟል ያሉት አቶ ኤልያስ አሁን ላይ ያለው ሕገወጥነት በቅርቡ ተግባራዊ ከተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያ በኋላ ወርቅ በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ባንኮች መግባት ጀምሯል ብለዋል።

አቶ ሚሊዮን፤ ባለፈው በጀት ዓመት 900 ኪሎ ግራም ወርቅ መገኘቱን አንስተው ከማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያ በኋላ በነሃሴና መስከረም ወር ብቻ ከሁለት ሺህ 700 ኪሎ ግራም በላይ ወርቅ ማግኘት መቻሉን ጠቁመዋል። ይህም የፖሊሲ ማሻሻው ያመጣው ውጤት መሆኑን ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ ከግብርናው በመቀጠል ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የምታገኘው ከማዕድን ዘርፉ ነው።

በቀጣይም በዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ለማሳደግ ሶስት የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካዎች በግንባታ ላይ ናቸው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው ፕጀክቶቹ በአንድ ዓመት ከግማሽ ጊዜ ውስጥ ተጠናቀው ወደ ማምረት ይገባሉ ብለዋል።

አቶ ሚሊዮን፤ የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካዎቹ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ በዓመት ከ10 ቶን በላይ ተጨማሪ የወርቅ ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል። ይህም ወደ ውጭ የሚላከውን የማዕድን ምርት በመጠንም ሆነ በጥራት እንዲጨምር ያደርገዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ፕሮጀክቶቹ በቤኒሻንጉል ፣ ጋምቤላና ትግራይ ክልሎች እንደሚገነቡ የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው በቤኒሻንጉል ክልል በኮርሙክ ወረዳ የሚገነባው ፕሮጀክት ትልቅና በዓመት እስከ ዘጠኝ ቶን ወርቅ እንደሚያመርት ተናግረዋል።

አቶ ሚሊዮን፤ ከሶስቱ ፕሮጀክቶች በተጨማሪ ጉጂ የሚገኘው ነባር የወርቅ ማምረቻ ኩባንያ የማስፋፊያ ሥራ እየተሠራለት መሆኑን ገልጸው ከወርቅ ባለፈም የፖታሽ ማዕድንን በአግባቡ ማምረት የሚያስችል ፕሮጀክቶች በአፋር ክልል የሚገነቡ ይሆናል ብለዋል።

በ2016 በጀት ዓመት ወደ ውጭ ከተላኩ ማዕድናት 420 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን ያስታወሱት ሚኒስትር ዴኤታው በዚህ ዓመት 800 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑንም አንስተዋል።

የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብቶች ዘርፉን እንዲያለሙ በሀገሪቱ ክፍት የሆነ አሠራር ተዘርግቷል። በዋናነት ከዘርፉ የውጭ ምንዛሬን በማግኘት የካፒታል ምንጭ እንዲሆን እየተሠራ ነው ብለዋል።

በተጨማሪ ከውጭ የሚመጡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመተካት ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን ማምረትና ለዜጎች የሥራ እድል መፍጠር በዘርፉ የሚሠሩ ሥራዎች መካከል ናቸው ሲሉ ገልጸዋል።

# የሰንደቅ ዓላማን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አጥንታቸውን ስለከሰከሱበት እና የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር ስለከፈሉበት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ሰንደቅ ዓላማችን ደም የፈሰሰበትና የሕይወት መስዋዕትነት የተከፈለበት በመሆኑ ለትውልዱ በአግባቡ ማሳወቅ ይገባል ያሉት ልጅ ዳንኤል መስፍን፣ ወላጆችም ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ የሰንደቅ ዓላማ ክብርን፣ የሀገርን ባህልና ታሪክ፣ የወደፊት አቅጣጫዎችን እያስረዱ መሆን እንዳለበት ተናግረዋል።

በትምህርት ቤትም ሰንደቅ ዓላማ ጨርቅ ነው ተብሎ የሚተው አለመሆኑን ማስረዳት ከተቻለ ኢትዮጵያን የሚመሩና ጋሻ የሚሆኑ፣ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ እና በማህበራዊ ዘርፎች እውቀት ያላቸው እንዲሁም ሀገርና ሰላም ወዳድ ዜጎችን ማፍራት ይቻላል ነው ያሉት።

የማንንም ልጅ እንደራሳቸው ልጆች የሚያስተምሩ እና ለትምህርት ፍላጎት ያላቸው መምህራንንም በማፍራት ሀገራችንን ካደጉ ሀገራት ጋር ተርታ ማሰለፍ፣ ታሪኳን እና ባህሏን ለዓለም ሕዝብ ማሳወቅ ይገባል ብለዋል።

ሚዲያዎችም ሰላምን የሚሰብኩ፣ የሀገርን ታሪክና ባህል የሚያጎሉና እውነታዎችን በአግባቡ ለህብረተሰቡ የሚያደርሱ በመሆን ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት የሰንደቅ ዓላማ ክብር የሀገርና የሕዝብ ክብር በመሆኑ ሲሰቀልና ሲወርድ ከሕዝቡ አልፎ ንጉሡ ነገሥቱ በመንገድ ላይ ካሉ ይቆማሉ። አሁንም ይህ መቀጠል አለበት ብለዋል።

በጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር የቀድሞው የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል ሻምበል ዋኘው ዓባይ ወልደማርያም በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የሰንደቅ ዓላማ ቀን የሚከበረው አባቶቻችን ለሰንደቅ ዓላማ ምን ያህል ታማኝ እንደሆኑ ለትውልዱ ለማስገንዘብ ነው።

ቀደም ባሉት ጊዜያት “ተመልከት ዓላማህን፣ ተከተል አለቃህን፣ አክብር ሰንደቅህን” እየተባለ እንደሚነገር አስታውሰው፤ ሰንደቅ ዓላማ የሀገር መለያ አርማ እና የሕገመንግሥቱ መጀመሪያ አንቀጽ ነው ብለዋል።

ቀደም ሲል ሰንደቅ ዓላማ ጠዋት 12 ስዓት ተሰቅሎ ማታ 12 ሠዓት ይወርድ ነበር። ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀልና ሲወርድ ማንም ከቆመበት አይነቃነቅም፣ መኪና አይነዳም፣ ከብቶች ይታገዳሉ ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜም ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣና ሲወርድ ሕዝብ መንቀሳቀስ የለበትም ተብሎ በአዋጅ መነገር አለበት። በዚህም የሰንደቅ ዓላማን ክብር ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲያውቁት ይሆናል ነው ያሉት።

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በቀለሞቿ ከዓለም የተለየች ናት። አረንጓዴው ልምላሜና ሀብት፣ ቢጫው ሰላምና ተስፋ፣ ቀዩ ደግሞ ጀግንነት እና መስዋዕትነትን የሚወክል መሆኑን አስታውቀዋል።

ሰንደቅ ዓላማን አባቶቻችን ጠብቀው አሁን ላለንበት ዘመን እንዳደረሱት ገልጸው፤ እኛም ሀገራችንን ለማስጠበቅ በዘመትንበት ቦታ ሁሉ የምናስቀድመው ሰንደቅ ዓላማን ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አባቶቻችን ሹመት ሲሰጣቸው ሰንደቅ ዓላማህን ጠብቅ፤ ሕገመንግሥትህን አስከብር ተብለው ይሰጣቸዋል። በአሁኑ ጊዜ ትውልዱ ሰንደቅ ዓላማን እንዲያከብሩ በትምህርት ቤቶች፣ በሚዲያዎች እና በሌሎች አማራጮች ስለሰንደቅ ዓላማ ክብር በስፋት መነገር እንዳለበት አብራርተዋል።

የሰንደቅ ዓላማ ቀንን በዓመት አንድ ቀን ከማክበር ባለፈም በትምህርት ቤቶች፣ በመሥሪያ ቤቶች፣ በሚዲያዎች የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሩን መዘመር እና ለሰንደቅ ዓላማው ክብር መስጠት እንደሚገባ አሳስበዋል።

የሰንደቅ ዓላማ ቀን ላለፉት 16 ዓመታት በጥቅምት ወር የመጀመሪያ ሳምንት ሰኞ የሚከበር ሲሆን ዘንድሮም 17 ኛው የሰንደቅ ዓላማ ቀን ዛሬ በሀገር አቀፍ ደረጃ ይከበራል።

# ሩዝ- ለኢኮኖሚ

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከማረጋገጥ ጎን ለጎን ለሩዝ ግብይት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ በማስቀረት ኢኮኖሚውን መደገፍ እንደሚችል ግምት ተሰጥቶታል።

የዓሳ ግብርና ተመራማሪና በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ረዳት ፕሮፌሰር አላየው ያለው ለኢፕድ በሰጡት ቃል፤ ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን ለመቻል ሩዝን ቀዳሚ አማራጭ የሰብል ዓይነት ማድረግ ተገቢ ነው።

ኢትዮጵያ በሩዝ ምርታማ ለመሆን በርካታ ምቹ ሁኔታዎች አሏት የሚሉት ዶክተር አላየው፤ ሰፊ መሬት፣ ተስማሚ የሆነ የአየር ንብረት እንዲሁም ሰፊ የውሃ አካል ያለው መሬት በዋናነት ተጠቃሽ መሆናቸውን ይናገራሉ።

ሩዝ በኢትዮጵያ በምግብ እራስን ለመቻል ለሚደረገው እንቅስቃሴ በእጅጉ ሊደግፍ የሚችል ከመሆኑም በላይ ኢኮኖሚውን ከማሳደግና የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘት አኳያ ያለው ሚና እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አለመሆኑንም ያብራራሉ።

በተለይ የሩዝ ምርታማነትን ማሳደግ ከሚኖረው የራሱ ጠቀሜታ በተጨማሪ የዓሳን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያግዝ እንደሆነም ነው የሚናገሩት።

በትንሽ መሬት ብዙ ምርት ማግኘት መቻሉና በተቀናጀ መልኩ ከዓሳ ሀብት ጋር በተመሳሳይ ቦታና ጊዜ የሚመረት በመሆኑ ሩዝን ከሌሎች ሰብሎች ተመራጭ ያደርገዋል ይላሉ።

ሩዝንና ዓሳን ጎን ለጎን እንዲመረቱ ማድረግ የሩዝ ምርታማነት እንዲጨምር እንደሚያደርግ በተለያየ ጊዜ በተደረገ ምርምር መታወቁንም ያክላሉ።

በሀገሪቱ በሩዝ ዘርፍ ያለውን ከፍተኛ አቅም አሟጦ ለመጠቀም ማህበረሰቡን ስለሩዝ አመራረትና አጠቃቀም ያለውን ንቃት ማሳደግ፣ በየአካባቢው ተስማሚ የሆኑ ዝርያዎችን በጥናት ማስደገፍና የተለያዩ ግብዓቶች በወቅቱ ማቅረብ ወሳኝ ነው ባይ ናቸው።

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር አላየው ገለጻ፣ እንደ ሀገር በሩዝ ዘርፍ የተጀመሩ ስራዎች ተስፋ ሰጪ ቢሆንም ሀገሪቱ ካላት አቅም አንጻር አሁንም ተጨማሪ ሥራዎች የሚፈልጉ ናቸው።

በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የግብርና ምጣኔ ሀብት ባለሙያና መምህር አማን ረቂቱ (ዶ/ር) በበኩላቸው ሩዝ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ በተጨማሪ ኢኮኖሚውን ከመደገፍ አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ይላሉ።

ሩዝን ማስፋፋት በጥቂት መሬት ምርታማ ከመሆን በተጨማሪ ሌሎች ሰብሎችን ለማምረት የሚወጣው ከፍተኛ ሀብትና ጊዜ ለመቆጠብ ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚሉት ዶክተር አማን፤ ሩዝ በተለይ ለሌሎች ሰብሎች የማይሆኑ ቦታዎች ላይ ስለሚበቅል እንዲሁም ምቹ የአየር ሁኔታ መኖሩ ይበልጥ ትርፋማ ያደርጋሉ።

ሩዝን ወደ ውጭ ገበያ መላክ ጠቃሚ ቢሆንም መጀመሪያ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውል በማድረግ እንደ ተኪ ምርት መጠቀም ቢቻል የበለጠ ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል መሆኑንም ይናገራሉ።

በተጨማሪም የሀገሪቷን የእርሻ ሥርዓት በመቀየር የተለመዱ ሰብሎችን ብዙ ጠቀሜታ ባላቸው ሰብሎች በመቀየር ኢኮኖሚውን መደገፍ ይገባልም ባይ ናቸው።

በሩዝ እርሻ በሚፈለገው ልክ ውጤታማ ለመሆን በዘርፉ ከዚህ በፊት እንደውስንነት የሚነሱ ጉዳዮች ምላሽ መስጠት፣ ምርት እንዳይባክን የተለያዩ ጥንቃቄዎች ማድረግ፣ የመፈልፈያ ማሽኖች ለአርሶ አደሩ ማቅረብ፣ የገበያ ትስስር መፍጠር እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መሥራት ለነገ የማይባል ቀዳሚ አጀንዳ ስለመሆኑ አጠራጣሪ አይሆንም።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰንደቅ ዓላማችን የአብሮነታችን ማሠሪያ፣ የአሸናፊነታችንም ማብሰሪያ ነው!

ሀገር በሕዝቦች፣ ሕዝቦችም በሀገር ይገለጻሉ፡፡ ኢትዮጵያ ስትታወስ ኢትዮጵያውያን መጠራታቸው፤ ኢትዮጵያውያን ሲታወሱም ኢትዮጵያ መወሳቷ የዚህ እውነት አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ይሄ የሀገር እና ሕዝብ የአብሮነት መጠሪያ፤ የስም መወራረስ የሚገልጠው የአይነጣጠሌነት ማኖሪያ ደግሞ አንድ ኃያል ምልክትና መወከያ ጉዳይ አለ፡፡

ይሄ መወከያ ዓርማ ደግሞ እንደየሀገራቱ ታሪክ፣ ሥልጣኔ፣ የጥበብና የልዕልና ደረጃ ገናንናነትን ይጎናጸፋል። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ባለ ታሪክ፣ ባለ ጥበብ፣ ባለ ገድል እና የነጻነት ቀንዲል የሆኑ ሀገራት ደግሞ ይሄ ዓርማቸው የእነርሱ ብቻ ሳይሆን የብዙሃን ምልክት ሆኖ ይወረሳል፡፡ ዛሬ ላይ ለዚህም ነው የኢትዮጵያ መታወቂያ ዓርማና ምልክት የሆነው ሰንደቅ ዓላማዋ በብዙ ሀገራት ሰንደቅ ዓላማ ውስጥ ቀለሙ ተቀይጦ የሚገኘው፡፡

ምክንያቱም ይሄ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ባለቀለም ጨርቅ ብቻ አይቀለም፡፡ ይልቁንም የነጻነት፣ የባለታሪክነት፣ የአልሸነፍ ባይነት፣ የድል አድራጊነት፣ ወራሪን የማሳፈር ጀብድና ባለገድልነት፣ የመተባበርና በሕብር የጸና አንድነት፣... ወካይ ማሕተም ነው፡፡ ቀለማቱም ቢሆኑ ቱባ ትርጓሜን የያዙ፤ በተስፋና ሕብር የደመቀ ተደማሪ ዓርማን ያዘሉ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ የሚታዩት ሦስት ቀለማት (አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀዩ)ን ብንመለከት፤ አረንጓዴው የሥራ፣ የልምላሜና የዕድገት ምልክት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ደግሞ በተፈጥሮ የታደለች፣ የአስራ ሦስት ወር ባለጸጋ፣ ቢያንስ ዘጠኝ ወራትን ዝናብ የምታገኝ፣ ዓመቱን ሙሉ በሚፈስሱ ወንዞቿ ዓመቱን ሙሉ ማምረትና ሕዝቦቿን መመገብ የሚያስችል ሀብት የታደለች ሀገር መሆኗን እንዲገልጽ ሆኖ በውክልና የተቀመጠ ነው፡፡

ቢጫውም ቢሆን፣ ኢትዮጵያ ያላትን ሀብት ተጠቅማ የመልማት እና የመበልጸግን፣ የትናንት ገናና ታሪክና ገድሏን መልሶ የመጎናጸፍንና ሌሎችም ከፍ የማለት ተስፋዎቿን፤ ለሕዝቦች ነጻነትና እኩልነት ምድርነቷን ብቻ ሳይሆን፣ ከትናንት እስከ ዛሬ ለሰው ልጆች ፍትሕ መስፈን የሠራች መሆኗን የተግባር ማንነቷን በወካይ ዓርማዋ ላይ ያኖረችበት ነው፡፡

ሦስተኛውና ቀዩ የቀለም ውክልናዋ ደግሞ፣ ኢትዮጵያ የነጻነት ምድርነቷን፤ ይሄ ነጻነት ደግሞ በኢትዮጵያውያን የደምና የሕይወት መስዋዕትነት የጸና ስለመሆኑ፤ እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ሆነ ነገ ለዚህ ነጻነት እና ለሕዝቦች እኩልነት ሰፍኖ መዝለቅ የሚደረግን የመስዋዕትነትና የጀግንነት ገድል የሚያመለክት ነው፡፡

በእነዚህ ሦስት ቀለማት ላይ አርፎ በመሃል ላይ የሚገኘውና ቢጫ ፍንጣቂ ብርሃንን የያዘው ባለ ሰማያዊ መደብ ክብ ዓርማ ደግሞ፤ ኢትዮጵያውያን ከትናንት እስከ ዛሬ ለአብሮነትና ነጻነታቸው ብቻ ሳይሆን ስለ ሰላማቸው ከፍ ያለ ዋጋ መክፈላቸውን፡፡ ዛሬም ሆነ ነገ በየትኛውም እንቅስቃሴያቸውና ተግባራቸው ሰላምን አስቀድመው የሚሠሩ የሚተጉ ስለመሆናቸው የሚናገሩበት ምልክታቸው ነው፡፡

ዛሬ ይሄን ዓይነት ከፍ ያለ የማንነት መግለጫ እና ወካይ የሆነውን ሰንደቅ ዓላማችንን ቀን ሰጥተን ስናከብረውና ስናስበው፤ እኛ ኢትዮጵያውያን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን፤ አብሮነትና ኅብረታችን፤ ወንድማማችነትና ፍቅራችን ከምንም በላይ ጸንቶ እንዲዘልቅ ዳግም ቃል የምናድስበት እንዲሆን በማድረግ ነው፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ፣ ኢትዮጵያ የትናንት ገናን ማንነቷን የሚመልሱ፤ ሙሉ ነጻነትና ሉዓላዊነቷን የሚያረጋግጡ ዘርፈ ብዙ የልማት ተግባራትን ለመከወን፤ የተጀመረውን ዘርፈ ብዙ የኢኮኖሚ ዕድገትና ስኬት ለማስቀጠል፤ እንደ ሀገርም እንደ ሕዝብም እንዲሆን የሚጠበቀውን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን በማድረግ ሂደት ውስጥ ሁላችንም ከእኛ የሚጠበቅብንን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችለንን ቁርጠኝነት ለመላበስ ሰንደቅ ዓላማችንን ጨብጠን ቃል የምንገባበት በመሆኑ ነው፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ለአብሮነታቸው፣ ለብልጽግናቸው፣ ለመልካም ጉርብትናና ትብብራቸው አቅም የሚሆነውን ሰላም ለማጽናት ሰንደቅ ዓላማቸውን አስቀድመው የሚናገሩበት መድረክ በመሆኑ ነው፡፡ በተለይ ዛሬ ላይ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በውስጥ የጥፋት ኃይሎች፤ በውጪ ደግሞ የኢትዮጵያን ከፍ ማለት የማይፈልጉ ታሪካዊ ጠላቶች ዙሪያችንን እያንገዋበቡ ባሉበት ወቅት፤ የሰንደቅ ዓላማውን ስሜት መላበስ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም ዘንድሮ ለ17ኛ ጊዜ የብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን "ሰንደቅ ዓላማችን ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጵያ ከፍታ!" በሚል መሪ ሃሳብ ስናከብር፤ አንድም የውስጥ አብሮነትና አንድነታችንን የማጽናት ቃላችንን በማደስ፤ ሁለተኛም፣ ኢትዮጵያ የልማትና የሕልውና ጥያቄዋን ለመመለስ ለምታደርገው ማናቸውም እንቅስቃሴዎች መንገዶቿ ሁሉ ሰላማዊና ትብብር መሆኑን በማሳየት፤ ሦስተኛም፣ የሰንደቅ ዓላማችን ክብርና ፍቅር ያልገባቸው ማናቸውም ኃይሎች ቢኖሩና የሰላም መንገድ እንቢኝ ቢሉ፤ የትናንቱ የኢትዮጵያውያን ገድል በዛሬው ትውልድ ደም ውስጥም ስለመኖሩ በማስገንዘብ ሊሆን ይገባል፡፡ ምክንያቱም ሰንደቅ ዓላማችን የአብሮነታችን ማሰሪያ፣ የአሸናፊነታችንም ማብሰሪያ የሚሆነው ይሄን በማድረግ ውስጥ ነው!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ</u>
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

<u>ዋና አዘጋጅ</u>
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

<u>አድራሻ</u>
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

<u>የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ</u>
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

<u>የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር</u>
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

<u>የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ</u>
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

<u>የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች</u>
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

<u>የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል</u>
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

<u>የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ</u>
ስልክ - 011-1-26-43-39

<u>ማከፋፈያ</u> ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የጥራት ደረጃን ከማውጣት በተጓዳኝ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግም ያስፈልጋል!

ክብረ መንግሥት

ጥራት ሰፊ እና ጥልቅ የሆነ ሃሳብ አለው። ለቃሉ ግልጽ ያለ ትርጉም ለመስጠት የማይቻልበት ሁኔታ የሚታይ ሲሆን፣ ለእዚህ ምክንያቱ በሁሉም ተግባር ውስጥ የማይገኝና በአንድ ነገር የማይወከል መሆኑ ላይ ነው። በምርት ብንለው፣ በአገልግሎት፣ በሰው ለሰው ግንኙነት ብንል በማኅበራዊ ትስስር በሁሉም ነገር ውስጥ ያለ ጽንሰ ሃሳብ ነው። ለዚህ ነው "quality is in everything you do in life" እየተባለ የሚገለጸውም።

እኔ ግን ከሰፊው ጽንሰ ሃሳብ አንዱን መዝገቤ ላወጋችሁ ነው። ይህም የንግድ ዘርፉን ይመለከታል። በዚህ እሳቤ ጥራት መለኪያና መመዘኛ (standards) ይቀመጥለታል። መለኪያዎቹ የብሔራዊ ደረጃዎች ድርጅት /international organization for standards (ISO)/ ሊሆኑ ይችላሉ። በኩባንያ ደረጃ በሚቀመጡ መለኪያዎችም (company standards) ሊመዘንም ይችላል።

እነዚህ መለኪያዎች ደግሞ እያንዳንዳቸው ይዘቱ ምን ላይ ነው የሚለውን ያመላክታሉ፤ እንደ ሀገር ከዘመኑ ጋር አብሮ እየዘመኑ መሄድን ያላምዳሉ፤ ዜጎችን ጠቅመው አካባቢን ይጠብቃሉ፤ ጊዜውን የዋጀ የኢኮኖሚ እድገት እንዲመጣም የበኩላቸውን ይወጣሉ። በጥራት አስቦ፣ በጥራት አምርቶ፣ ምርትን በጥራት ሥራ ላይ እንዲያውሉም እድል ይሰጣሉ። ከምንም በላይ ብክነትን በመቀነስ ተወዳዳሪነትን በማስፋት የገቢ ምንጭን ከፍ ያደርጋሉ።

ሀገራችን ከዚህ አንጻር ምን ሠራች ካልን ሁለት ነገሮችን መሥራቷን በዋናነት መጥቀስ እንችላለን። የመጀመሪያው እንደ ሀገር ጥራት የምትፈትሽባቸው ሁኔታዎቹ ተዘጋጅተዋል፤ እነዚህም የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ከብሔራዊ የደረጃ ዝግጅት ቴክኒክ ኮሚቴ ጋር በመሆን ያወጣቸውና በብሔራዊ ምክርቤት የጸደቃቸው 285 የሚደርሱ ብሔራዊ ደረጃዎች ናቸው።

እነዚህ ደረጃዎች በስድስት ዘርፎች የተዘጋጁም ሲሆኑ፤ በግብርናና በምግብ ዝግጅት 18፣ በመሠረታዊና አጠቃላይ የደረጃ ዝግጅት 28፣ በኬሚካልና ኬሚካል ውጤቶች 72፣ በኮንስትራክሽንና ሲቪል ኢንጂነሪንግ 79፣ በኤሌክትሮ ሜካኒካል 69፣ እንዲሁም በአካባቢና ጤና ደህንነት 19 ደረጃዎች እንደሆኑም የደረጃዎች ኢጀንሲ ያወጣው መረጃ ያመለክታል። በእነዚህ ደረጃዎች በመጠቀም ሀገራት በዓለምአቀፍ ደረጃ ምዘና ምርቶችን ሲያሰራጩ ኢትዮጵያም የራሷ በሆኑ ብሔራዊ መመዘኛዎች ምርቶችን ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ታደርግባቸዋለች። ወደውጪ የሚላኩትንም ምርቶች የቅድመ ጭነት ኢንስፔክሽን ሥራዎችን ታከናውንባቸዋለች።

ሌላው ኢትዮጵያ ገና በማደግ ላይ ያለች ሀገር በመሆኗ በብሔራዊ ደረጃዎቿ ብቻ የገቢና ወጪ እቃዎች (ምርቶች)ን ጥራት ማረጋገጥ ስለሚያዳግታት የጥራት ቁጥጥርን በአማራጭ የምትሠራበትን መንገድም አመቻችታለች። ይህም በዓለምአቀፍ ደረጃ እውቅና ያላቸውን የቅድመ ጭነት ኢንስፔክሽን (Pre-Export Verification of Conformty) አድራጊ ኩባንያዎችን በመጠቀም ጥራትን የምታረጋግጥበት ነው። እነዚህ ኩባንያዎች Cotecna እና Bureau Veritas የሚባሉ ሲሆኑ፤ ሥራቸውን የጀመሩት ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ በሶላር ቴክኖሎጂ እና በውሃ ፓምፕ ምርቶች ላይ ነው። ምርቶቹ ሲገቡ የቅድመ ጭነት ኢንስፔክሽን ሥራዎችን በማከናወን የማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣሉ። በቅርቡ በወጣ መረጃ ደግሞ ተጨማሪ 11 ምርቶችን የሚያረጋግጡና የጥራት ሰርተፍኬት የሚሰጡ ይሆናል።

ጥራት ለኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በተለይም ለአምራች ኢንዱስትሪውና ለንግድ ተወዳዳሪነት አቅም መጎልበት ሁነኛ መፍትሄ ነው። ከኅብረተሰቡ ጤናና ደህንነት አንጻርም ጉልህ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። አቅራቢዎች ወይም ተቀባዮች በበቂ ሁኔታ አቅማቸው እንዲያድግ፣ ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር ከማድረግ አኳያ ሚናው ቀላል የሚባል አይደለም። ምክንያቱም ወጪዎቻቸውን በመቀነስና የሚያቀርቧቸውን ምርቶች ጥራት በመጨመር ገቢያቸውን ያሳድጋሉ። ይህ ሲሆን ደግሞ ሀገርም በከፍተኛ ሁኔታ እድገቷን ታፋጥናለች።

**ድንገተኛ ፍተሻዎች እንደ ተጨማሪ ግብዓትነት ታይተው ሊሠራባቸውም ይገባል፡፡ ምክንያቱም ዛሬ ላይ በሀቅ ከሚሠራው ይልቅ በውሸት የሚሠራው ተቀባይነትን እያገኘ ያለበት ሁኔታ ይታያል**

ለአብነት ከደረጃ አንጻር ብናነሳ የግብርና መሣሪያዎችን የተመለከቱ 51 ደረጃዎች መዘጋጀታቸው የግብርና ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ፤ ከማዘመን አልፎ የግብርና ምርትን ወደ ውጭ እስከመላክና ገቢን ከፍ እስከማድረግ ድረስ የሚዘልቅ ጥቅም ያስገኛሉ።

ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተገናኘ የተዘጋጁ ስድስት ደረጃዎችም እንዲሁ የሚሰጡት ጥቅም በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም። ከቆሻሻ መለየት፣ ማስወገድና መልሶ መጠቀም ጋር የተቆራኙ ጥቅሞችን እንድናገኝ ያስችላሉ። በአጠቃላይ ጥራት የምርቶችን፣ የአገልግሎቶችንና ተያያዥ ጉዳዮችን ጥራት ከማሻሻልና ከማረጋገጥ አንፃር ፋይዳው የጎላ ነው።

ይህ ግን እውን የሚሆነው ሕግ ወይም ደረጃ ብቻ ስለወጣ እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል። መሬት ላይ በተግባር በሚገባ የሚተረጎምበት ሁኔታ ይወስነዋል። ከዚያ የላቁ ደጋፊ ሥራዎችም አብረውት ሊከናወኑ ይገባል። ለአብነት ተግባራዊነቱ ታችኛው ማህበረሰብ ክፍል ድረስ መውረዱንና እየተሠራበት መሆኑንን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ድንገተኛ ፍተሻዎች እንደ ተጨማሪ ግብዓትነት ታይተው ሊሠራባቸውም ይገባል። ምክንያቱም ዛሬ ላይ በሀቅ ከሚሠራው ይልቅ በውሸት የሚሠራው ተቀባይነትን እያገኘ ያለበት ሁኔታ ይታያል። በገቢም እየተሻለ የሚሄደው አመሳስሎ በመሥራት ሕዝቡን የሚያጭበረብረው ነው። ገበያውን የሚያጨናንቀውም ይሄው አካል ነው።

ለዚህ ችግር መፈጠር ምክንያቱ ደግሞ ተጠያቂነት አለመስፈኑ ነው። የተወሰኑ ርምጃዎች ቢኖሩም ሕዝቡ ከተበዘበዘና ነገሮች ከተጠናቀቁ በኋላ ነው። ለዚህ አብነት የሚሆነን በቅርቡ የታገደው የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ቁስ ሲሆን፤ ማከፋፈያው ማህበረሰቡ ዘንድ ደርሶ ካለቀና ተጠቃሚው በገንዘብም ሆነ በሌሎች አገልግሎቶች ጉዳቶች ከተሰቃየ በኋላ ነው። ይህ ደግሞ ሌቦችን ያበረታታል እንጂ ሀገርንም ሆነ ዜጋውን ሊጠቅም አይችልም፤ እንዲያም ጉዳት ነው የሚያደርሰው።

እናም ደረጃዎች ከማውጣት ጎን ለጎን ፍተሻው፤ ክትትሉ ከስር መሠረቱ ሊሠራበት ይገባል። ወቅቱን የዋጀ ክትትል በተቆጣጣሪው አካል መደረግ ይኖርበታል። በተለይም ድንገተኛ ፍተሻዎችን መጠቀም ከምንም በላይ ያስፈልጋል። ሕግ ሲጣስም ተገቢውን ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። በእርግጥ ተቆጣጣሪው አካል ብቻ ይህንን ያስፈጽም አይባልም። ማህበረሰቡ ይህን ሕገወጥ ተግባር ለማስወገድ የበኩሉን ርብርብ ማድረግ ይኖርበታል።

ጊዜውን የጠበቀ ቁጥጥርና ሕግን የማስከበሩ ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥልም የዚሁ የማህበረሰቡ ተባባሪነት ወሳኝነት አለው። ተቆጣጣሪው ተቋም የእያንዳንዱን ችግር ለይቶ ለማወቅ የሚችልበት አጋጣሚ አይኖርምና የችግሩ ሰለባ እየሆነ ያለው የዚሁ ማህበረሰብ ሃላፊነት ወሳኝ ነው። በተለይ ግለሰቦች ነገሮችን አብጠርጥሮ ማውጣት ስለሚችሉ የጥራት አምባሳደር ሆነው ሕግ እንዲከበር መሥራት ይገባቸዋል በማለት ሃሳቤን ቋጨሁ። ሰላም!!

# መካሪና አስታራቂ የግብረገብነት እሴቶቻችን የት ሄዱ?

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)

ኢትዮጵያ ሀገራችን ከተፈጥሮ ሀብቷ እኩል በባሕል ሀብቷም ምስጉን ሀገር ናት። ሰውነትን ባስቀደሙ፣ አብሮነትና ወንድማማችነትን ባጸኑ መካሪና ዘካሪ፣ አግባቢና አስታራቂ የአብሮነት ባሕሎች የበለፀገች መሆኗ እሙን ነው። በአንድ ግንድ ላይ እንዳቆጠቆጡ ቅርንጫፎች ኢትዮጵያዊነት የተደነቀባቸው ቱባ ባሕሎች ባለቤቶች ነን። ልዩነትና ቅያሜ በሌላቸው ቢኖራቸውም ከኢትዮጵያዊነት ባልበለጠባቸው የታሪክ ገድል ስር ፊተኞች ነበርን።

ኢትዮጵያዊነት በልጦብን ጥልና አለመግባባትን በይቅር ለግዜር ስንፈታ፣ ቅያሜና ቁጣን በይቅርታ ስናበርድ ታሪክ አለን። ወንድማማችነት ልቆብን ልዩነቶቻችንን በምክክር፣ ጥያቄዎቻችንን በምክክር ስናስታርቅ ገድል አለን። ለተገፋውና ፍትሕ ለራቀው መልከ ጥቁር ድምፅ ሆነን አፍሪካን ነፃ ስናወጣ ‹የፍትሕ ደሴት› የሚል ስም ተችሮን ነበር። በኮንጎ፣ በኮሪያና በኩባ ሠላም አስከባሪዎች ሆነን ስንሰለፍ ‹የሠላም ዘቦች› የሚል መጠሪያ ነበረን። አፍሪካን በጠቅላላና የዓለምን አንድ ሁለተኛ የሚሆን ሕዝብ ከባርነት አላቀን፣ ፍትሕና እኩልነት እንዲሰፍን በማድረግ ለተወጣነው ኃላፊነት ዛሬም ተመስጋኞች ነን።

እኚህ ሁሉ የድልና ገድል ታሪኮቻችን ደምቀው የተጻፉት በማኅበራዊ ሥርዓታችን በኩል ነው። ሀገርና ሕዝብ በቀደሙበት፣ ከምንም በላይ ደግሞ ለሠላምና ፍትሕ ቀናዒ መሆናችን ያመጣው ክስተት ነው። ተያይዘንና ተደጋግፈን የነበረንበት ዘመን ተለያይተው የነበሩን ጎረቤት ሀገራት አንድ አድርጓል። በእኛ እውነት፣ በእኛ ጽናት፣ በእኛ ፍትሕ፣ በእኛ ፍቅር ከባርነት ነፃ የወጡ ሀገራት ብዙ ናቸው።

ዛሬስ? አይደለም ለሌላው ለራሳችንም አልሆንም። ለምን ካልን የመጀመሪያው ሰውና ባለክብር ካደረጉን ባሕልና እሴቶቻችን ርቀናል። የሚበልጠውን ትተን የማይጠቅመንን መከተል ጀምረናል። ሠላም አጥተን በጦርነት የናወዝነው፣ ሀይ ባይ ጠፍቶ በእርስ በርስ መገዳደል ዋጋ እየከፈልን ነው።

ፖለቲካ የሰዎች አስተሳሰብ ቢሆንም እሳቤው ሀገርና ትውልድ ከሌለበትና ራስንና ጥቂት ቡድኖችን የሚጠቅም ከሆነ ውሎ አድሮ ጦርነትን መፍጠሩ አይቀርም። ከዓፄው ወደአብዮታዊ መንግሥት ስንመጣ፣ በዘመነ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያዊነት እየደበዘዘ ዘረኝነት እየተስፋ ሲመጣ አላስተዋልንም። ዘረኝነት በአንድ ያቆመንን፣ አስተሳስሮና አጋምዶ ያጸናንን ወንድማማችነታችንን ሲናጠቀን አልነቃንም።

ኢትዮጵያ የሚለውን ስም በዓለም ያስተዋወቀልንን ጨዋነትና ግብረገብነትን ሽሮ ሌላ የጥላቻ መንፈስ ሲወልድ ተኝተን ነበር ፤ እነሆ በዛ መንፈስ ዛሬም ድረስ በኃይል እና በይዋጣልን ዋጋ እንከፍላለን። ለሽምግልና ቁጭ ያልንባቸው ዋርካዎቻችን ተሲያት ውጧቸዋል። በአንተም ተው በአንተም ተው የአባቶች ግሳጼ ፍቅር ያበጁ ሸንጎዎቻችን በዝምታ ጸልመዋል።

ለምን ዝም አልን? በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ አለመናገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ አውቀነዋል? እነዛ ዝምታዎች ግን ዛሬ ላይ ዋጋ እያስከፈሉን ነው፤ ሰው ተረት ፈጥሮ የብቻ ትርክት ሲተርክ አዋቂዎች ለምን ዝም አሉ? ማንም እየተነሳ ያልበላውን ሲያክ፣ አብሮነትን የሚሸረሽር የዘረኝነት ወግ ሲያወጋ መለኞች ለምን ዝም አሉ?

መናገር..መነጋገር አለብን። መወያየት እውነትን መግለጥ አለብን። በእርቅና በይቅርታ ጸቦቻችንን ንቀን ወደፊት መገስገስ ይኖርብናል። ሀገር የሠሩ ማኅበራዊ ትስስሮቻችን በዝምታ ደብነው ወደማይነሱበት እንጦሮጦስ የገቡ ቀን ብንናገር እንኳን ላንደመጥ እንችላለን። በእውነትና በብዙኃን ሀሳብ ሀገር የምናቀናበት ጊዜው አሁን ነው። ሠላሳ ዓመታትን ፖለቲካው እያወራ ሕዝብ እያዳመጠ መጣን። ሦስት አስርት ዓመታትን ፖለቲከኞች ያሻቸውን እየተናገሩ ሕዝብ የጉዳይ አስፈጻሚ ሆኖ ከዛሬ ደረስን። ይሄው ዛሬ የዝምታችንን ፍሬ እንበላለን።

> **ሲያስታርቁንና ሲያስተቃቅፉን የነበሩ ዋርካዎቻችን የሉም..። አዛውንቶቻችን ለመናገር ድፍረት አጥተዋል። ጥላዎቻችን ላይ ተሲያት ፈንጥቋል። እርቅ ሜዳችን ላይ ጠራራ ወድቋል። ለዘረኝነት መደራጀት የለብንም። ለጥላቻና ወንድማማችነትን ለመሸረፍ መቧደን አይኖርም። ዳግም በሥርዓቶቻችን በኩል እንብቀል**

ፖለቲከኞቻችን ዝም ብለው ሕዝብ እንዲናገር መድረክ ይበጅ። መንግሥት ሲናገርና ሕዝብ ሲናገር የተለያየ ነው። ድሃና ኋላ ቀር እንዲሁም በጦርነትና በዘር ሽኩቻ በደበነች ሀገር ላይ ሕዝብ ተናጋሪ መንግሥት አድማጭ ነው መሆን ያለበት። ያለፉትን ሠላሳ ዓመታት ሕዝብ ተናግሮባቸው ቢሆን ኖሮ ለዚህ ሁሉ ጣጣ ባልበቃን ነበር። እንደብሔራዊ ምክክር ያሉ የብዙኃን አፎች የሚሰሙበት መድረክ ዋጋው የላቀ ነው። ሳይቃጠል በቅጠል በሚል መርሕ ዝምታችንን ሰብረን፣ እልኸኝነታችንን ጥለን ለእርቅና ለምክክር እንቀመጥ።

ሲያስታርቁንና ሲያስተቃቅፉን የነበሩ ዋርካዎቻችን የሉም..። አዛውንቶቻችን ለመናገር ድፍረት አጥተዋል። ጥላዎቻችን ላይ ተሲያት ፈንጥቋል። እርቅ ሜዳችን ላይ ጠራራ ወድቋል። ለዘረኝነት መደራጀት የለብንም። ለጥላቻና ወንድማማችነትን ለመሸረፍ መቧደን አይኖርም። ዳግም በሥርዓቶቻችን በኩል እንብቀል።

እኛ ካልሄድንባቸው ሥርዓቶቻችን ምንም ናቸው። ባሕልና ወግ በሕዝብ በኩል የሚገለጹ እንጂ በራሳቸው የሚንጸባረቁ አይደሉም። በዘረኝነት የለወጥናቸውን፣ በትላቻ የሸሸናቸውን አስታራቂና አዋሓጅ እሴቶቻችንን ዳግም መቃኘት ያስፈልጋል።

አባቶቻችን ዛሬ ላይ ድሮን ሲያጡ ‹የዛሬን አያድርገውና› ብለውስ ወጋቸውን ይጀምራሉ በሁሉም ወጎቻቸው ውስጥ ይሄ አባባል አይጠፋም። ፊታቸውን አጠይመው፣ መልካቸውን አወይቦ ይሄን ያክል ያስከፋቸው ዘመን፤ በጥላቻና በዘረኝነት የጨቀየው የኛ ዘመን ነው። የድሮ ናፋቂ ያደረጋቸው ።

ስለቀደመው ዘመን ፍቅር፣ መተሳሰብ፣ አንድ የመሆንን እውነታ ሲተርኩ ተረት ፈጥረው የሚያወሩት እንጂ እውነት አይመስልም ነበር። ‹ይብላኝ ለእናንተ በዚህ ጉድ ዘመን ለተፈጠራችሁ እኛስ ደግ ዘመን አሳልፈናል› ብለው ስለኛ ነገዎች ሲያስቡ እና ሲቆዝሙ ማየት የተለመደ ነው ።

በዓለም ላይ ካሉ ድንቅ የፍልስፍና አስተምሕሮች መሐል ‹እኛ ሁላችንም የምርጫዎቻችን ውጤቶች ነን እንጂ በእኛ ላይ የሚሆነው ነገር ውጤቶች አይደለንም› የሚለው አስተምሕሮ ብዙ ጊዜ ውስጤን ይይዘዋል። አስተምሕሮ ዘርዘር አድርገን ስናየው እንዲህ ነው። በሕይወት በኩል ካየንው በሕይወት ውስጥ የደረሰብን መከራ ሳይሆን ለመከራው የምንሰጠው ምላሽ ነው ወደነገ የሚያራምደን እንደ ማለት ነው።

እንደስኬት ካስተዋልነው ደግሞ ስኬት ማለት በተንገዳገዱ ቁጥር ወደኋላ ማፈግፈግ ሳይሆን ተግዳሮትን ለድል መወጣጫነት መጠቀም የሚለውን ይይዛል። አሁን ካለው የሀገራችን አሁናዊ ሁኔታ ጋር ሲተያይ ደግሞ ጦርነትን ምርጫችን በማድረጋችን ዋጋ በመክፈል ላይ እንገኛለን። በቃ ካልን፣ በመነጋገር ለመግባባት ከተቀመጥን ነገሮች የሚስተካከሉ እንደሆኑ የሚጠቁም አስተምሕሮ ነው።

እውነት ነው ብዙ ነገሮች እንዲጎዱን በይሁንታ ፈቅደንላቸው ዋጋ እያስከፈሉን ይገኛሉ። ጦርነትን ስለመረጥን ሠላም አጥተናል። ዘረኝነትን ስላስቀደምን ኢትዮጵያዊነትን ተነጥቀናል። ባሕልና ሥርዓቶቻችን በነውር ተውጠው መገዳደል ተራ ነገር ሆኗል። በቃ ባለማለታችን ወይም ደግሞ ለመነጋገር ባለመፍቀዳችን ሞትና ጉስቁልና የእለት ተዕለት ዜናዎቻችን ሆነዋል።

እስኪ በቃ እንበል። ጦርነት በቃ እንበል። ጥላቻ፣ ዘረኝነት ይብቃን እንበል። ሠላምና ወንድማማችነትን እንዲጎመሩ የመገፋፋት ልማዶቻችንን እንተው። ያኔ ያለመጠራጠር ሠላም ይመጣል። እርቅ ይወርዳል። የእምነታችንን ፍሬ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ በአንድ ፎሌ እንመገባለን።

ግብረገብነት የዘመናዊነት ራስ ነው። ሥልጣኔ ብዙ መነሻዎች ቢኖሩትም እንደጨዋነት ግን አይሆኑም። ሥልጡን ስንባል ታሪክ የጻፈን፣ በሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ ፊተኞች ሆነን ስንጠራ ሰብዓዊነትን ከአብሮነት ጋር በቀየጠ ሥርዓት በኩል ነው። ሳይገባን ወደአውሮፓና ወደምዕራባውያን እንመለከታለን እንጂ እውነተኛ ሥልጣኔ ያለው በታሪኮቻችንና በባሕሎቻችን ውስጥ ነበር።

ይሄን ለማረጋገጥ የታሪክ መነሻችንን መቃኘት መልካም ነው። በባሕልና በሥርዓት እንደዳበረ ሀገር አስፈሪ የለም። ከጦር መሣሪያ በላይ ሥርዓትና ጨዋነት በአንድ ሀገር ላይ አስፈሪ ነው። ምንም ሳይኖረን አቻችለውና አፋቅረው ያኖሩን መልካም ባሕሎቻችን ናቸው። አሁንም ከእርስ በስር ግፊያ ወጥተን ሠላማዊቷን ኢትዮጵያ ለመፍጠር ሥልጣኔያችንን አብሮነትን ማድረግ ይኖርብናል። በአባቶች አስታራቂነት፣ በባሕልና ሥርዓቶቻችን መሪነት ተጋፍተን ከመውደቃችን በፊት ልንያያዝ ይገባል።

ዘረኝነት መርዝ ነው። ጥላቻ እሳት ነው። ለጊዜው እንጂ ሁላችንንም መብላቱ አይቀርም። እነዛ ሰብዓዊነትን የተማርንባቸው፣ አብሮነትና ፍቅርን የተቋደስንባቸው፣ የፍትሕና የሚዛናዊነት ወኔዎቻችን ዛሬ ላይ በብሔር ካባ ባይወይቡ ኖሮ በልማትና በእድገት ፊተኞች በሆንን ነበር። በባሕል ታርቀን፣ በሥርዓት ተገርተን ስለሰው ልጆች ግድ የሚሰጠው ማንነታችን ዛሬም ነፍስ ይዝራ።

በተፈጥሮና በግብረገብነት ከበለፀጉ ጥቂት የዓለም ሀገራት አንዷ ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት። በዚህ ስምም ለዘመናት ተጠርተንበታል። የተፈጥሮ ሀብታችንን ወደእድገትና ሥልጣኔ በመቀየር ላይ የምንታማ ቢሆንም ሀገር የሠራንበት የባሕል ሃብታችን በብሔር ወይቦ ዘረኝነትን ማቀንቀን እስከጀመረበት ጥቂት ዓመታት ድረስ ኢትዮጵያዊነትን ገንብተንበታል። አሁንም የሚበጀን ከዘረኝነት ማጥ መውጣት ነው።

የነበረውን ሽሮ የሚመጣውን የሚቀበል የጋራ ትርክት እንፍጠር። ፍቅርን የሚቀበል፣ አብሮነትን የሚዋጅ ብዙኃነትን ያቀፈ የተግባቦት ታሪክ በእጅጉ ያስፈልገናል። የጥላቻ ስብከቶቻችንን ትተን ስለሠላምና ስለእርቅ አንደበቶቻችንን እናስላ። ጥላቻ የመጣንበትን የጦርነት ታሪክ ከመድገም ባለፈ የሚሰጠን ሌላ ክብር የለም።

በጋራ ትርክት ውስጥ የበለፀገ ሥርዓት የላቀ ዋጋ አለው። ፖለቲካችን ከዚህ ቢጀምር፣ ፖለቲከኞቻችን ከዚህ ቢነሱ ለጦርነት የሚሆን ሞራል አይኖረንም ነበር። ትውልዱም በፊተኞቹ ፈር ላይ አንጋጦ የጥላቻ ሰንፈጥን ባላነፈነፈ ነበር።

የሥነምግባርና የግብረገብነት አስተምሕሮች በብዛትና በጥራት መኖራቸው ትውልዱን በፍቅርና በኢትዮጵያዊነት አርቀው ጭምት ከማድረግ ባለፈ ሀገርና ሕዝብን በተመለከተ ዋስትና የሚሰጡን ጉዳዮች ናቸው። ሁላችንንም የሚያግባባ እውነት ልጥቀስ ብል ልጠቅስ የምችለው በጨዋነትና በሥነሥርዓት የተገነባውን የኢትዮጵያዊነት ወግ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ሥርዓትና ጨዋነት ነው። አስተዳደጋችን፣ አስተሳሰባችን፣ ማኅበራዊ ልምምዳችን፣ አኗኗራችን፣ ባሕል ወጋችን ከዚህ እሳቤ ውስጥ የተቀዳ ነው። ተቀድተን ግን አልባከንም በሥርዓትና በጨዋነት በሥነምግባርም የታረቀውን ወግ አጥባቂ ሀገርና ሕዝብ ፈጥረናል። ይሄ መሆኑ ያጎደለብን አንዳች እንደሌለ የሚያስማማን ሲሆን በምትኩ በእምነትና በፈሪሐ እግዚአብሄርም በልፅገን ከፉን እንድንጸየፍ አድርጎናል።

አሁን ላይ እነዛ ፀዓዳ መልኮቻችን ተገፈው ከመከባበር ወደመደፋፈር፣ ከመቻቻል ወደ ይዋጣልን ገብተናል። እነኚህም ከውርደት ባለፈ ምንም እንዳላበረከቱልን ያለፉት ዓመታቶች የዓይን እማኞቻችን ናቸው። በአንድ ጥላ ስር ለአንድ ጉዳይ የሚመክረው የጨዋነት ሥነምግባራችን ወይቦ ዋጋ እያስከፈለን ነው።

ልዩነታችንን ረስተን በአንድነትና በቤተሰባዊ መንፈስ ተቀላቅለንና ተዋሕደን የኖርንባቸው ጊዜያቶች ዛሬ ላይ ይናፍቁናል። ዘመን የሰው ልጅ የሀሳብ ባሪያ ነው። ድሮና ዘንድሮ በእኛው የአስተሳሰብ ሚዛን አምረውና ጎሽው ታዩ እንጂ እንደነበሩ ናቸው። በበጎ ሃሳብ በጎ ሀገር መፍጠር መጪውን አስተካክሎ ነገን የተሻለ ማድረጊያ ብቸኛ ዋስትናችን ነው። እንዳንበጠስ ሆነን የተገመድንው፣ እንዳንላላ ሆነን የጠበቅንው በአብሮነት ባሕሎቻችን በኩል ነው። እናም ሀገር ለሰጡን የጋራ ሥርዓቶቻችን እንገዛ።

# የእንስሳት መኖ ፍላጎትን ለመመለስ የተሰማራው ማኅበር

**አስቴር ኤልያስ**

ኢትዮጵያ የቀንድ ከብት ሃብቷ በዓለምም ሆነ በአፍሪካ ደረጃ ከፊተኛዎቹ ተርታ ላይ እንድትገኝ አርጓታል። ይህንን ሃብት ለኢኮኖሚ እድገቷ በመጠቀም ረገድ ግን እዚህ ግባ የሚባል ሥራ እንዳልሠራች ይታወቃል። ለዚህ ዋና ዋና ምክንያቶች ከሚባሉት መካከል በእንስሳት ጤና ላይ አለመሠራቱ፣ በምርምርና በዝርያ ማሻሻል እንዲሁም የድርቅ አደጋ መከላከል ላይም እንዲሁ ብዙ ርቀት መሄድ አለመቻሉ ይጠቀሳሉ።

የእንስሳት መኖን በጥራትና በበቂ ሁኔታ ማቅረብ አለመቻልም ሌላው አንዱ ምክንያት ስለመሆኑም ይገለጻል። የእንስሳት መኖን ለእንስሳቱ ማቅረብ አለመቻል ከእንስሳት የሚገኘውን ምርትና ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል። ድርቅ በሚመላለስባት ሀገር፣ ለእንስሳት መኖ ትኩረት ሰጥቶ አለመሥራት ችግሩን ምን ያህል ውስብስብ ሊያደርገው እንደሚችል መገመት አይከብድም። ያለ እንስሳት መኖ ሥጋ በሚፈለገው ልክና ጥራት ማግኘት አይቻልም፤ ወተትና እንቁላልም እንደዚያው።

ሀገሪቱ በግብርናው ዘርፍ ለእንስሳት ሀብት ልማት እያከናወነች ካለችው ተግባር በተጓዳኝ በሌማት ትሩፋት እየተሠራ ያለው ሥራ የመኖን አስፈላጊነት አውጥቶ አሳይቶታል። ዜጎች በዚህ መርሐ ግብር በወተት፣ በዶሮና እንቁላል ልማት ላይ መሠማራታቸው እየሰፋ ሲመጣ ትልቁ ችግር ሆኖ የመጣው የመኖ እጥረት ነው።

ይህን ችግር የተመለከተው መንግሥት ውስን የነበሩት የመኖ ማዘጋጃና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች እንዲበራከቱ ወደ ማድረግ እንዲገባ አርጎታል። ለእዚህም ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር በተከናወነው ተግባር በአሁኑ ወቅት በክልል ከተሞች የመኖ ማቀነባበሪያዎች ተገንብተው ወደ ሥራ ገብተዋል። የግል ዘርፉም እንዲሁ ይህንኑ እንዲያደርግ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለታል። ዜጎች በማኅበር እየተደራጁ በእንስሳትና እንስሳት ተዋፅዖ ልማት ከመሠማራታቸው በተጨማሪ በመኖ ልማት እየተሠማሩም ይገኛሉ።

ሰሞኑን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድን ወደሸገር ከተማ አስተዳደር በማቅናት ኮዬ ፈጬ እና ገላን ጉዳ ክፍል ከተማ በተለያዩ ወረዳዎች እየተካሔደ የሚገኘውን የተቀናጀ የከተማ ግብርና ልማትን ተዘዋውሮ ተመልክቷል።

በጉብኝቱም በዳለቲ ወረዳ ገላን ጉዳ ክፍለ ከተማ የሚገኘውን ሙስሊምና ሶፍያ የእንስሳት መኖ አምራች ማኅበርን እንቅስቃሴ ቃኝቷል። የማኅበሩ ሊቀመንበር ወጣት ሙስሊም ናስር እንደሚናገረው፤ ማኅበሩ አምስት አባላትን ያካተተ ነው፤ ከእነዚህም መካከል ሦስቱ ወንዶች ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው።

በማኅበሩ ከተደራጁት ውስጥ ሦስቱ በቻይና የከፍተኛ ትምህርታቸውን ተከታትለው ዲግሪ ይዘዋል። ወደ እንስሳት መኖ ማምረት የመግባታቸው ምስጢርም በቻይና ለአራት ዓመት ያህል ለትምህርት በቆዩበት ወቅት በኢትዮጵያ እና የቻይና መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ማስተዋላቸውና ይህም ቁጭት ያሳደረባቸው መሆኑ ነው።

በቻይና እና በኢትዮጵያ ያለውን የዶሮ ሥጋ አመጋገብ ሲያስተውሉ በጣም የተራራቀ ልዩነት እንዳለው መረዳታቸውን የጠቀሰው ወጣት ሙስሊም፤ ‹‹በቻይና በጣም በትንሽ ገንዘብ የዶሮ ሥጋ በቀን ሦስቴ መብላት ይቻላል፤ የዶሮ ሥጋ በኢትዮጵያ እንደሚታየው እንደ በቀላሉ የማይደረስበት አይነት ትልቅ ምግብ አይታይም›› በማለት ይናገራል። ኢትዮጵያን ሲያስቡ ደግሞ የዶሮ ሥጋ እንኳን በየጊዜው ሊበላ ቀርቶ በበዓል ወቅትም በናፍቆት አሊያም ልዩ ዝግጅት ሲኖር የሚቀርብ የምግብ አይነት መሆኑ ያስገርመው እንደነበር ያነሳል።

ይህን በሁለቱ ሀገሮች በዶሮ ሥጋ ላይ የሚታየውን እጅግ ሰፊ ክፍተት የተመለከቱት እነ ወጣት ሙስሊም ክፍተቱን መሙላት የሚቻለው እንዴት ነው? ሲሉ ብዙ አሰቡ፤ በጉዳዩ ላይ ተወያዩናም ሕልማቸውን እውን ለማድረግ ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ዶሮ ማርባት



ቀዳሚው ተግባራቸው እንደሆን ደመደሙ። ወደ ሀገር ቤት ከተመለሱ በኋላ በቀጥታ ወደ ዶሮ እርባታው ከመግባታቸው በፊት ሁኔታዎችን ተዘዋውረው ለማቃኘት ሞከሩ። በምልከታቸውም በብዙዎቹ የዶሮ አርቢዎች ዘንድ በተግዳሮትነት የሚነሳው የዶሮ መኖ ጉዳይ እንደሆነ ተገነዘቡ።

ቆም ብሎ ማሰብ የግድ መሆኑን መረዳታቸውን ወጣቱ ጠቅሶ፤ ‹‹ወደ መጀመሪያው የዶሮ እርባታ ሥራቸው ከመግባታቸው በፊትም በትኩረት ተወያይተናል›› ሲል ይገልፃል። ስለዚህም ከመሠረቱ መነሳት ግድ እንደሚል በመገንዘብና እቅድ በማውጣት የመጀመሪያ ሥራቸው መሆን ያለበት የዶሮ መኖ ማምረት እንደሆነ መግባባት ላይ መድረሳቸውንም ያስታውሳል።

‹‹ሦስት ዓመት ያህል አስፈላጊ የሆኑ ማሽኖችን ከውጭም ከሀገር ውስጥም የምናገኝበት ሁኔታ አጠናን። እንዴትና በምን እንደምንሠራ መዘገጃጀት ጀመርን፤ ተዘዋውረንም ተጨማሪ ጥናት አደረግን›› በማለትም ያስረዳል። ለጥቂት ዓመታት በመኖ ምርት ላይ ተሠማርተን ውጤታማ ከሆንን ጎን ለጎን ዶሮም ማርባት እንጀምራለን ወደሚል ውሳኔ ደርሰው መኖ የሚያለሙበትን መንገድ መያያዝ መጀመራቸውን ያመለክታል።

‹‹ሐሳባችን እና እቅዳችን ሰፋ ያለ ነው፤ ዶሮ እርባታ ብንገባ ምርታችን ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ የሚውል ሳይሆን ሥጋው ታሽጎ ወደ ውጭ ሀገር መላክንም የሚጨምር ነው›› የሚለው ወጣት ሙስሊም፤ ይህም የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ከሌላው ሃገር ተሞክሮ መውሰዳቸውን ያስረዳል።

የእንስሳት መኖ አምራች ማኅበር መመሥረታቸውን የሚናገረው የማኅበሩ ሊቀመንበር፣ አሁን የእንስሳቱን መኖ የማምረት ሥራውን ተያይዘውታል። በኢትዮጵያ ያለው ገበያ ሲታይ በጣም ተፈላጊ መሆኑን መረዳታቸውንና በእንስሳት መኖ ማምረት ላይ መንግሥት በእጅጉ ሲያበረታታም እንደሚታይ ይናገራል።

እርሱ እንደሚለው፤ ለየትኛውም ሕይወት ላለው ነገር ምግብ ወሳኝ ነው፤ ሁሉም ነገር የሚነሳው ከምግብ ነው። ሰውን ጨምሮ ዶሮ፣ የወተት ከብትም ሆነ የሚደልብ ሰንጋ ሁሉ ምግብ ያስፈልገዋል። በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ከፍተኛ እንደመሆኑ ለዚህ ሕዝብ የሚመጥን ምግብ ማቅረብ መቻል ፈታኝ ነው። አሁን ካለው 120 ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ እንስሳት ለሚያረባው 10ና 20 ሚሊዮን ሕዝብ መኖ ማድረስ ቢቻል ለመኖ አምራቾች ትልቅ ገበያ እንደሚፈጠር አብራርቷል።

‹‹ወደ ምርቱ የገባነውም ይህን ታሳቢ በማድረግ ጭምር ነው፤ ደግሞም ውጤታማ እንሆናለን ብለን አስበናል›› ሲል የሚናገረው ወጣት ሙስሊም፤ ከተለያየ ቦታ ብዙዎች የእንስሳት መኖ ጥያቄን እያቀረቡ መሆኑን ይገልፃል። በመሆኑም በርካታ የመኖ ማምረቻ አስፈላጊ



**ወጣት ሙስሊም ናስር**

መሆኑ አጠያያቂ እንዳልሆነ ይጠቅሳል።

የእንስሳት መኖ ማምረቻ ማኅበራቸውን ለመመሥረት ሲነሱ ሁለት ሚሊዮን ብር ይዘው መሆኑን ይናገራል። በማምረቻ ሼዱ ውስጥ የሚገኙት ማሽኖች ደግሞ ብዙ ብር የወጣባቸው መሆናውን ይገልፃል። ከእነዚህ ማሽኖች መካከል እስከ 12 ሚሊዮን ብር የወጣበት ማሽን እንደሚገኝ ያስረዳል።

‹‹ከእንስሳት ጋር ተያይዞ በተለይ በቀንድ ከብት ከፍተኛውን ቁጥር በአፍሪካ ደረጃ የያዘችው ኢትዮጵያ ናት›› የሚለው የማኅበሩ ሊቀመንበር፤ ‹‹ለዚህ የቀንድ ከብት ሀብታችን ተገቢውን መኖ ካለማቅረባችን የተነሳ በምርቱ በኩል ውጤታማ መሆን አልቻልንም›› ሲል ቁጭቱን ይናገራል። ለኢትዮጵያ ልማት ባንክ ምስጋና ይድረሰውና በዚህ ላይ ብድር በማመቻቸት ረገድ ድጋፍ እንዳደረገላቸው ጠቅሶ፣ ይህም ሥራቸውን ለማቀላጠፍ እንደረዳቸው ያመለክታል።

‹‹በዳለቲ ወረዳ ማምረቻውን ከመክፈታችን በፊት፤ ከፍተኛ ወጪ ወጥቶበት የተገዛው ማሽን ውጤታማ ይሆን ዘንድ ወሳኝ ቦታ ስንፈልግ ቆይተናል፤ የተለያዩ ቦታዎችን ለማግኘት ጥያቄ አቅርበን ነበር። ጥያቄያችን እስከ ሻሸመኔ ድረስም ዘልቆ ነበር›› በማለት ያስታውሳል። ይሁንና ሳይሳካላቸው መቆየቱን ያስረዳል።

በመጨረሻም በሸገር ከተማ አስተዳደር በገላን ጉዳ ክፍለ ከተማ በዳለቲ ወረዳ ውሃና መብራት እንደልብ የሚገኝበት የተመቻቸ ሼድ ስለመገኘቱ ሐሳብ ይቀርብላቸዋል። ‹‹እኔ በቦታው ተገኝቼ ባየሁ ጊዜ ሁሉም ጥሩ መሆኑን ስለተረዳሁ ሥራ ጀመርን፤ የመብራት መቆራረጥም አላጋጠመንም›› ሲል በጅማሬያቸው ወቅት የነበረውን ሒደት ያብራራል።

‹‹ሼዶቹ ውስጥ ለውስጥ የተሟላ መንገድ ያላቸው ከመሆናቸውም በተጨማሪ፤ የሚገኙትም ከተማው አካባቢ እንደመሆኑ ወደ ከተማ ለመድረስም የሚወስደው ጊዜ አጭር ነው። ስለሆነም ክፍለ ከተማው ችግር እንዳይኖር ጥሩ ሥራ እየሠራ ነው›› ሲል ያብራራል።

ወጣቱ ሙስሊም እንደሚለው፤ የእንስሳት መኖ የራሱ ይዘት ያለው ነው፤ በተለይ ደግሞ የዶሮ መኖ ዘጠኝ ያህል ግብዓቶችን ይፈልጋል፤ ለመኖነት የሚዘጋጀው እነዚህ ሁሉ ተደበላልቀው ነው። ከዘጠኙ ግብዓቶች ስምንቱን በሃገር ውስጥ ማግኘት ይቻላል፤ ግብዓቶቹን መግዛት አስቸጋሪ ሊሆን የሚችለው የተሟላ ፋይናንስ ሳይኖር ሲቀር ነው።

ከግብዓቶቹ መካከል 50 በመቶ የሚሆነው በቆሎ መሆኑን ጠቅሶ፤ ይህም በኢትዮጵያ በስፋት የሚመረት መሆኑ ምቹ ሁኔታ እንደተፈጠረላቸው ይገልጻል። ‹‹በቆሎ በስፋት ከሚመረትበት ከትውልድ አካባቢዬ ኢሉባቡር አስመጣለሁ›› ይላል። ቫይታሚን የሚባለው ግብዓት ግን ከውጭ ሀገር የሚመጣ መሆኑን አመልክቶ፣ ካለው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ጋር ተያይዞ ትንሽ አዳጋች እንደሆነባቸው ይገልጻል። ‹‹ግብዓቱን አስመጪዎችም የሚሸጡልን ሦስትና አራት እጥፍ አትርፈው በመሆኑ በዚያ በኩል ችግር አለብን›› ሲልም ጠቁሟል።

‹‹ወደፊት በመኖ ሥራ ላይ ብቻ ተንተርሰን አንቀጥልም፤ ጎን ለጎን ብዙ ሥራዎችን ለመሥራት አስበናል›› የሚለው ወጣት ሙስሊም፤ እንደጅምር በአሁኑ ሰዓት ከእንስሳት መኖ ጎን ለጎን ፍየል የማደለብ ሥራ በመሥራት ላይ መሆናቸውን ያመለክታል። ለጊዜ የጀመሩት ጥቂት ፍየሎችን በማደለብ እንደሆነ ገልፆ፤ ይህንንም በማስፋት ወደ ዶሮ እርባታ ለመግባት ማቀዳቸውን ይጠቁማል። ‹‹በተለይም የሥጋ ዶሮን ማርባት ነው ትልቁ ፍላጎታችን ነው›› ሲል ይናገራል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የዶሮ ሥጋ መብላት የቅንጦት ያህል እንደሚቆጠር ጠቅሶ፣ ‹‹በየእለቱ በሚኖረን የምግብ ገበታ ውስጥ ዶሮን ማግኘት ብርቅ ነው፤ እኛ ግን ይህን የመቀየር ሕልም ጭምር እንዳለን መናገር አፈልጋለሁ። ይህን ማድረግ ደግሞ እንችላለን ብለን እናምናለን›› በማለት ይናገራል።

መኖ እስካለ ድረስ ዶሮንም ሌሎች እንስሳትንም ማርባት ብዙ ከባድ እንደማይሆን ጠቅሶ፣ ‹‹የእኛ ሕልም የሥጋ ዶሮ በሰፊው በማርባት የራሳችንን ብራንድ በማድረግ አሸገን የዶሮ ሥጋ መሸጥ ነው። ይህን በአጭር ዓመት ውስጥ እናሳካዋለን ብለን እናስባለን›› ሲል የማኅበሩ ሊቀመንበር ጠቁሟል። በአሁኑ ወቅት እያመረቱ ያሉትን የእንስሳት መኖ የሚሸጡት በተለያዩ አካባቢዎች ባሏቸው ወኪሎች በኩል መሆኑን ጠቅሶ፣ ከእነዚህም መካከል ቱሉ ዲምቱ እና ቢሾፍቱ ያሉት ወኪሎች እንደሚጠቀሱ ተናግሯል። ጅማ ላይም ወኪል እንደሚፈልጉ ጠቁሟል።

በሌላ በኩል ከአዳማ ወደ ጂቡቲ በሚደረገው የቁም እንስሳትን ባቡር የማጓጓዝ አገልግሎት የእንስሳት መኖ ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ተናግሮ፣ የማኅበሩ አባላት ይህንንም ታሳቢ ያደረገ ሥራ መሥራት እንደሚፈልጉ ጠቅሷል።

‹‹በወኪሎቻችን ዘንድ የምንሸጠው የእንስሳት መኖ በኩንታል 4 ሺ 500 ብር ነው። ለእንቁላል ጣይ ዶሮ ማምረት የምንችለው ስድስትና ሰባት አይነት ነው። ለወተት ከብቶች የሚውል መኖ በአካባቢያችን ላሉ ሼዶች በመሸጥ ላይ እንገኛለን›› ይላል። የአንዱ ኩንታል መኖ ዋጋም እስከ ሦስት ሺ 400 ብር እንደሆነ ያመለክታል።

እሱ እንዳለው፤ እነ ወጣት ሙስሊሙ በመኖ ማምረቻው ለዘጠኝ ሰዎች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፤ ከድርጅቱ ሠራተኞች መካከል የማሽን ኦፕሬተርና የኒውትሪሽን ባለሙያ ይገኙበታል፤ የኒውትሪሽን ባለሙያው መኖው እንዴት ለእንስሳቱ መስጠት እንደሚገባ ግንዛቤ ይሰጣል። በተለይ በመኖ አሰጣጥ ለላይ በትኩረት ይሠራል፤ ደንበኞች ግንዛቤው እስኪኖራቸው ድረስ ማስረዳቱ ላይ ይሠራል። ምክንያቱም ለእንስሳቱ መኖ በገፍ መስጠት አያስፈልግም፤ በየስንት ሰዓቱ፣ እንዴት መሰጠት አለበት? የሚለው ትልቁ ነገር ነው። ለእንስሳቱ መኖ በገፍ መስጠት ለሞት ሊዳርጋቸው ጭምር ይችላል። ለእዚህም ምርታቸው የሚደርስበት ቦታ ሁሉ እየተዘዋወረ ባለሙያው ግንዛቤ እንደሚሰጥ አስታውቋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ልሣነ- ብዙነት እና ሥርዓተ ትምህርት

ገርማ መንገሥቴ

በ"አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ" ሥርዓት ስብራትና ውልቃት ከደረሰባቸው የትምህርት አንጓዎች አንዱ የቋንቋ ትምህርት ነው።

"አዲስ" (ከሱ በፊት የነበረውን ያረጀ፣ ያፈጀ፣ ለትምህርት ጥራት ብዙም አስተዋፅዖ የማያደርግ ወዘተ ለማለት ነው) በዚህ ሥርዓት ወደ ዳር ተገፍተው ከነበሩት የትምህርት አይነቶች አንዱ ቋንቋና ከሱው ጋር ተያይዘው የነበሩት የሥርዓተ ትምህርቱ አካላት እንደነበሩ አይዘነጋም። ይህ ደግሞ፣ በተለይ በድረ 1983 ዓ.ም ጎልቶ ይታይ የነበረ፤ እስከ ዛሬም የዘለቀ፣ ለመግባባትም ጭምር እያስቸገረ ያለ ርዕሰ-ነገር ነው።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የትምህርት ተቋማትን መልሕቅ አልባ አድርጎ በማንሳፈፍ ግራ ሲያጋባ የነበረው ይኸው የቋንቋ ትምህርት እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። የግል ትምህርት ቤቶች እንግሊዘኛን "ተደብቀው" እስከ ማስተማር ከመንግሥት ደንብና መመሪያ እንዲሸፍቱ ሲያደርግ የነበረው ይሄው ምክንያቱ በግልፅ ባልሰፈረው "እንግሊዝኛ እንዳታስተምሩ" ቀጭን ትእዛዝ እንደ ነበር የትምህርት ባለ ድርሻ አካላት ሁሉ በሀዘኔታ የሚናገሩት ጉዳይ ነበር። የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ፣ በአሁኑ ዘመን የዓለም እውቀት ታጭቆ የሚገኘው በዋናነት እንግሊዘኛ ቋንቋ ውስጥ ሆኖ ሳለ እሱን አለማስተማር ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ግራ ቢያጋባም።

ባለፈው በተባለው የትምህርት ሥርዓት መምህራንን ሲያተራምስና ወዲህና ወዲያ ሲያንከራትት የነበረው፤ የክልሎችን የትምህርት ቢሮዎችን እጅጉን ሲያስጨንቅ፣ የዘርፉ እምብርትና አስኳል የሆኑትን ተማሪዎችን ተረጋግተው በመቆም ትምህርታቸውን ይከታተሉ ዘንድ የሚያስችላቸውን የስበት ኃይል ሲያሳጣ የነበረው ከሁሉም በላይ ይኸው የቋንቋ ትምህርትና የ"ቋንቋ ፖለቲካ" ነበር ።

በዚህ በ"ሰነድ ፍተሻ" ዘዴ በተደራጀና በተዘጋጀ ጽሑፍ አማካኝነት ለመፈተሽ እንደምንሞክረው፣ ጉዳዩ ከሀገራትም አልፎ ዓለም አቀፋዊ ገፅታ ያለው ዐቢይ ርዕስ ነው።

"ካለፉት ጊዜያት በመማር ደካማ የሆነ የትምህርት ዝግጁነት እና አሰጣጥን ለማሻሻል" እየሠራ ከሚገኘው ትምህርት ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ከትምህርት ዓበይት የሪፎርም ትኩረቶች አንዱ የሥርዓተ ትምህርት ሪፎርም ነው።

አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት አንድ ተማሪ ሦስት (3) ቋንቋዎችን እንዲናገር የሚያስችል መሆኑን በሚኒስቴሩ የተፈጥሮ ሳይንስ ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ኃላፊ ዛፏ አብርሃ በቅርቡ ለብዙኃን መገናኛ ገልፀዋል።

በሥርዓተ ትምህርቱ ችግሮች ዙሪያ ከመምህራን፣ ከወላጆች እና ከተማሪዎች የሚነሱ ሀሳቦችንም እንመለከታለን ያሉት የዝግጅት ክፍሉ ኃላፊ፣ ተማሪዎች በቅድመ አንደኛ ደረጃ በአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ በአንደኛ ደረጃ ዓለም አቀፍ ቋንቋ ማለትም እንግሊዝኛ ከዚያም ከሦስተኛ ክፍል በኋላ ሌላ የአጎራባች ክልል ቋንቋ እንደሚማሩም ተናግረዋል።

ሥርዓተ ትምህርቱ በምሑራን ጥናት ላይ ተመሥርቶ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ መዘጋጀቱ በተነገረለት በዚህ ሰነድ ላይ እንደተብራራው፤ የአጎራባች ክልል ቋንቋዎችም በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሳይሆን በክልሎች የሚመረ(ጡ)ጥ ነው የሚሆነው።

እዚህ ላይ "ትምህርትንና የቋንቋዎች ብዛትን አያይዞ ማቅረብ ለምን አስፈለገ?" የሚል አስተያየት አዘል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል። ከተነሳ መልሱ በጣም አጭርና ግልፅ ነው። እሱም ሁሉንም የዘርፉን ምሑራን ያግባባውና "ከአንድ ቋንቋ (Monolingualism)፣ ወይም ሁለት ቋንቋ (Bilingualism) ይልቅ ብዙ ቋንቋዎችን ማወቅ (Multilingualism) ጠቀሜታው እጅግ የላቀ"፤ በተለይም በሥርዓተ ትምህርቱ ተካትተው በትምህርት አይነትነት ሊሰጡ የሚገባቸው የመሆኑ ጉዳይ ነው።

ይህ ሁሉ መንደርደሪያ ተማሪዎች የተለያዩ ቋንቋዎችን መማርና ማወቅ ያለባቸው መሆኑን፤ የትምህርት ፖሊሲውም ሆነ እየተከናወነ የሚገኘው ሪፎርም፤ እንዲሁም ሥርዓተ ትምህርቱ የቋንቋ ትምህርትን በተመለከተ ተገቢውን ትኩረት ሊሰጡ የሚገባቸው ስለ መሆኑ፤ ዘመኑ፣ በተለይም መጪው ዘመን (የወጣቶቹ ነውና) በአንድ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን ሊስተናገድ የሚችለው በተለያዩ ቋንቋዎች እውቀትና ክሂል ነውና ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ ተማሪዎችም ሆኑ ማንኛውም የትምህርት ባለ ድርሻ አካል ሊያውቅ የሚገባ መሆኑን ለማስረፅ ነው።

የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች እንደሚያሳዩት ዛሬ ዓለም ላይ የተለያዩ ቋንቋዎችን ማወቅ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ ነው። ልክ የእኛኑ አማርኛ ሀገራት እየተሻሙና ባለሙያዎችንና የወደፊት ዲፕሎማቶቻቸውን ከወዲሁ እያፈሩበት እንዳሉት ሁሉ፤ እኛም የተለያዩ ቋንቋዎችን ለማወቅ መጣር፤ መጪው ትውልድም ከፊቱ እየመጡ ያሉ ዕድሎች ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ እንዲያውቅ ማድረግ፤ ማስተማር ግዴታ ይሆናል።

ይህንን ስንል ዛሬ፣ የተለያዩ ዕድሎችን ይዞ እየመጣ መሆኑ እየተነገረለት ያለውን ቻይኒኛ (ማንድሪን) ለመማር ዓለም እየተሰለፈ ይገኛል። ዓለምን እንግሊዝኛ ቋንቋ ሲመራ እንዳልነበረ ሁሉ ቻይኒኛን አስቀድሞ ተከታይ ለመሆን ያለው ጊዜ ሩቅ አይመስልም። ዛሬ የተለያዩ ሀገራት ዜጎች ቻይኒኛን በማወቅ ከሥራ ጀምሮ የተለያዩ ዕድሎች ተጠቃሚ ለመሆን አጫጭር ኮርሶችን በመማር ላይ ናቸው።

ፖለቲካን ከቋንቋ ነጥለው ማየት የቻሉ ሀገራት፣ በተለይም የአውሮፓ ሀገራት ከአንድ በላይ ቋንቋዎችን በሥርዓተ ትምህርታቸው ውስጥ በማካተት ዜጎቻቸውን የብዙ ቋንቋዎች ተናጋሪ (መልቲሊንጉዋል) የማድረግ ሥራዎችን መሥራት ከጀመሩ ቆይተዋል። የሀገር ውስጦችንም ሆነ የሌላ ሀገራት ቋንቋዎችን በማስተማር ብቁ ዜጋ ማፍራት ለነገ የሚባል ሥራ አለመሆኑን በመገንዘብ ትምህርት ቤቶች የቋንቋዎች መገኛ ብቻ ሳይሆን መፍለቂያ እስኪመስሉ ድረስ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር አጣጥመው እያስኬዱት ይገኛሉ።

የተለያዩ (የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ) ቋንቋዎችን ማወቅ ጥቅሙ የትየለሌ መሆኑ የገባቸው ሀገራት የዓለምን ተጨባጭ ሁኔታና ይዞታ፤ እንዲሁም የወደ ፊት አቅጣጫ ከወዲሁ በመረዳት (ወይም፣ ስትራቴጂካሊ በማሰብ) በርካታ ዜጎቻቸውን እያበለፀጉና እያበቁ ይገኛሉ።

ጉዳዩን ያላደጉት ችላ ይበሉት እንጂ ያደጉቱ ግን ሥራዬ ብለው እየሠሩበት የሚገኙ ሲሆን፤ ለዚህም የአውሮፓ ኅብረት ሀገራት ተገቢ ማሳያዎች ከመሆንም በላይ ምሳሌዎች ናቸው።

መረጃዎች (ለምሳሌ "ዩሮኒውስ") እንደሚያሳዩት፣ የበለፀጉት የአውሮፓ ሀገራት ሁለትና ከዛ በላይ የውጪ ቋንቋዎችን (ፈረንሳይኛ፣ ጀርመንኛ፣ ጣሊያንኛ፣ እንግሊዝኛ ወዘተ) በማስተማር ረገድ "ግሩም" የሚባል ሪከርድ እያስመዘገቡ ሲሆን፣ ይህም ከዓመት ዓመት እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል።

ከላይ የጠቀስነው የመረጃ ምንጭ እንደሚያስረዳው፤ ሀገራቱ በሁሉም (ከቅድመ-መደበኛ ትምህርት እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት) የትምህርት እርከኖች የቋንቋ ትምህርቶችን አብዝተው የሚሰጡ ሲሆን፣ ከ2013 ጀምሮ እስከ 2022 ድረስ ባሉት ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ እመርታን እያሳዩ፤ ከልሳነ ብዝኃነት አኳያ የኋልዮሽ ሄደው የነበሩትም እያገገሙና ወደ ተሻለ ውጤት እየመጡ ናቸው ። ከመካከለኛ ደረጃው እንጀምር።

በመካከለኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ የውጪ ቋንቋዎችን የማስተማር እድገት በ2013 ከነበረበት 58.4 በመቶ በ2022 ወደ 60.7 በመቶ ደርሷል።

ከ2013 ጀምሮ እስከ 2022 ባለው ጊዜ ውስጥ በእነዚሁ የአውሮፓ ሀገራት ሁለትና በላይ የውጪ ቋንቋዎችን በማስተማር ሽፋናቸውን ከ4 ነጥብ 6 ወደ 6 ነጥብ 5 ከመቶ ማሳደጋቸው ተመዝግቧል።

**የተለያዩ ቋንቋዎችን ማወቅ በረከት እንጂ መርገምት ሆኖ አያውቅም:: በተለያዩ ቋንቋዎች መጻፍም ሆነ ማንበብ፤ የተለያዩ ቋንቋዎችን መስማትም ሆነ መናገር በብዙ እርምጃዎች ከሌሎች ቀድሞ መሄድ እንጂ የኋልዮሽ ጉዞ አይደለም:: የተለያዩ ቋንቋዎችን ማወቅ ስመ-ጥር ያደርጋል እንጂ ከሰው በታች አያደርግም፤ ያስመሰግናል እንጂ አያስወቅስም**

በ2022 በእነዚሁ የአውሮፓ ኅብረት ሀገራት የቋንቋ ማስተማር ሽፋናቸው በሁለት ተከፍሎ የተመዘነ ሲሆን፣ እንግሊዝ 98፣ ጣሊያን 96፣ ግሪክ 96 በመቶ ሽፋን ላይ በመድረስ በ"ከፍተኛ" ስር የተመደቡ ሲሆን፤ አየርላንድ (6 ነጥብ 1)፣ ሀንጋሪ (6 ነጥብ 6)፣ አውስትራሊያ (7 ነጥብ 7 ከመቶ ) ደግሞ በዝቅተኛ ውጤት አስመዝጋቢነታቸው ተለይተዋል።

በ2022፣ በአውሮፓ ኅብረት ሀገራት ውስጥ ካሉ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች መካከል 6 ነጥብ 5 ከመቶ የሚሆኑት ሁለትና ከዛ በላይ የውጭ ቋንቋዎችን ይማራሉ።

በሉዘንበርግ 79 ነጥብ 6 በመቶ የ1ኛ ደረጃ ተማሪዎች የውጪ ቋንቋዎችን በመማር እየመሩ ሲሆን፣ ላቲቪያ 37 ነጥብ 2 በመቶ፤ ግሪክ 34 ነጥብ 9 በመቶ፤ ኢስቶኒያ 33 ነጥብ 6 በመቶ ሽፋን በመስጠት እንደየቅደም ተከተላቸው ተቀምጠዋል።

እነዚህን ስኬቶች እናንሳ እንጂ፣ ልሳነ ክለኤነትንም ሆነ ልሳነ ብዙነትን በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ከማካተት አኳያ የወደቁና ከወደቁበትም የተነሱ ሀገራት እንዳሉ መዘንጋት አይቻልም። ፖላንድ ነጌቲቭ 6.8 በመቶ፣ ሉግዘንበርግ ነጌቲቭ 42 በመቶ እና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል።

እነዚህን ማሳያዎች እዚህ ማስቀመጥ ያስፈለገበት ዐቢይ ምክንያት አንድም የዓለም ሕዝብ ከግማሽ በላይ ልሣነ ክለኤ መሆኑ፤ እንደ ሀገርም ሲታይ አብዛኞቹ ሀገራት ልሣን ብዙ በመሆናቸው ነው። ችግሩ "አንዱ የአንዱን ምን ያህል ያውቃል?" ነው እንጂ ኢትዮጵያም እንደ አገር ልሣነ-ብዙ ሀገር መሆኗ ይታወቃል።

ላለፉት ዓመታት፣ እዚህ በመዲናችን አዲስ አበባ ለበርካታ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ እንግሊዝኛ እንደ አንድ የቋንቋ ትምህርት አይነት እንዳይሰጥ መደረጉ (ከዘንድሮ ጀምሮ የመማሪያ መጻሕፍት ሁሉ ተዘጋጅቶለት እንዲሰጥ ተወስኗል) አግባብ አለመሆኑን፤ እንዲሁም፣ ትምህርት ሚኒስቴር እያካሄደ ያለውን ሪፎርም ተከትሎ "ተማሪዎች በቅድመ አንደኛ ደረጃ በአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ በአንደኛ ደረጃ ዓለም አቀፍ ቋንቋ ማለትም እንግሊዝኛ፤ ከዚያም ከ3ኛ ክፍል በኋላ ሌላ የአጎራባች ክልል ቋንቋ እንደሚማሩ" መወሰኑን ለማፅደቅ ነው።

"ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች የተለያዩ የቋንቋ ተናጋሪዎች የሚኖሩባት ትልቅና ብዝኃነት ያላት ሀገር ነች፡፡" የሚለውን የራሱ የትምህርት ሚኒስቴር ሰነድ ("አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሐ-ግብር") መግቢያ ዓረፍተ ነገርንም ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባትና "አንድ ኢትዮጵያዊ ስንት የሀገሩን ቋንቋ(ዎች) ይችላል?" የሚለውን ጥያቄም ለማንሳትና ተማሪዎቻችን ከአንድ በላይ የብሔረሰብ ቋንቋ(ዎች)ን መማር ያለባቸው መሆኑን ማሳሰብ ነው።

በአሁኑ በማኅበረሰባችን፣ በተለይም በፖለቲካው ማኅበረሰብ ዘንድ ሁሉም የራሱን ቋንቋ እንዲማር እንጂ የሌላውን እንዲያውቅ ያለማበረታታት ሁኔታዎች ናቸው የሚታዩት። ይህ ጽሑፍ እንደዚህ አይነቶቹ አስተያየትና አስተሳሰቦች ታርቀው በዘመነ ግሎባላይዜሽን ሁሉም ብዙ ቋንቋዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጪ እንዲያውቅና የመጪ ሕይወት ዕድሉን ከወዲሁ እንዲያሰፋ ያበረታታል።

ኢትዮጵያ ይህንን ካደረገች በ1972 "የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ በማካሄድ ከዩኔስኮ" International Reading Association literary prize" የተባለ "ሽልማት" እንዳገኘችው ሁሉ አሁንም ባለብዙ ልሳን ትውልድ በመፍጠርም ከእነ ዩኔስኮ ሽልማት ማግኘቷ የማይቀር ይሆናል።

በመጨረሻም፣ የተለያዩ ቋንቋዎችን ማወቅ በረከት እንጂ መርገምት ሆኖ አያውቅም። በተለያዩ ቋንቋዎች መጻፍም ሆነ ማንበብ፤ የተለያዩ ቋንቋዎችን መስማትም ሆነ መናገር በብዙ እርምጃዎች ከሌሎች ቀድሞ መሄድ እንጂ የኋልዮሽ ጉዞ አይደለም። የተለያዩ ቋንቋዎችን ማወቅ ስመ-ጥር ያደርጋል እንጂ ከሰው በታች አያደርግም፤ ያስመሰግናል እንጂ አያስወቅስም።

ከዚህ አኳያ ነው እንግዲህ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንግሊዝኛ ቋንቋ እንዳይሰጥ ተደርጎ መቆየቱን የምናወግዘው። እውቋ የግብፅ ንግሥት ኪሊዮፓትራ ውብቷ፣ የአመራር ችሎታዋ ብቻ አልነበረም ለዝናዋ መነሻና ለተራዘመ እውቅናዋ መሠረት የሆናት፤ ከዘጠኝ ቋንቋዎች በላይ አቀላጥፋ መናገርና መስማት ብቻ ሳይሆን በቋንቋዎቹ መጻፍና ማንበብ መቻሏም እንጂ። ወደ እኛም ሀገር ስንመጣ በርካታ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ሥራዎች ጥለውልን ያለፉት እውቅ ሰዎች ቢያንስ ከአንድ በላይ ቋንቋዎችን የሚችሉ መሆናቸውን መገንዘብ ጠቃሚ ነው።

ከላይ የጠቀስነው የትምህርት ሚኒስቴር ሰነድ "በዝቅተኛ የትምህርት ደረጃዎች መሠረታዊ ክሂሎቶች ካላዳበሩ፣ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው፣ በአማርኛና በእንግሊዝኛ አቀላጥፈው እንዳይማሩ ከማድረጉም በተጨማሪ፣ በተከታታይ ደረጃዎች ባሉት ክፍሎች በሚማሩዋቸው የትምህርት አይነቶች ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ የዝቅተኛ ክፍል ደረጃ የንባብ ዳሰሳ /EGRA/ ውጤትን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሰባት የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች አዲስ ሥርዓተ ትምህርት የተነደፈ ሲሆን፤ በዚሁ ሥርዓተ ትምህርት መምህራን እንዲሠለጥኑና የመማሪያ ቁሳቁሶች ተመርተው እንዲከፋፈሉ ተደርጓል።" የሚል አንቀፅ አለው። ይህ አንቀፅ ይኑረው እንጂ ያ ሰነድ ለአደባባይ ከበቃ ከስንት ዓመት በኋላ እንኳን እንግሊዝኛ ቋንቋ ከሥርዓተ ትምህርቱ እንዲነቀል ተደርጎ እንደ ገና (በዚህ ዓመት) ተመልሶ ተተከለ። ይህ አይነቱ ስህተት ሊደገም አይገባም።

# ሕገ ወጥ ስደትና የዜጎች እንግልት

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

የስደት አስከፊነት መነገር ከጀመረ ረዥም ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ሆኖም ዛሬም ድረስ ባለማወቅም ይሁን የመጣውን ለመቀበል በመወሰን ሀገራቸውን ጥለው የተሻለ ኑሮ ፍለጋ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ቁጥር እያሻቀበ ነው። ከየቤቱ ለስደት የሚነሱ ዜጎች በተለይም ወጣቶች መንገድ ሲጀምሩ በይፋ ሳይሆን በድብቅ ነው። ምክንያቱም በርካቶች ለጉዞ የሚመርጡት ሕጋዊውን መንገድ ባለመሆኑ ከተጠያቂነትና ከአከላካይ ለመጠበቅ ሲሉ የሚያደርጉት ነው።

በአንጻሩ ወደ መዳረሻቸው በማቅናት በመንገድ ላይ እያሉ አልያም በየደረሱበት ሀገራት ችግር ሲገጥማቸው በሚደረግ የትብብር ጥሪ ቤተሰብ ማኅበረሰብና ሕዝብ የጉዳዩ ተካፋይ ሲሆን ይስተዋላል። ዛሬ ዛሬ በመንግሥት ከፍተኛ ርብርብ ከነበሩበት የስቃይ ሕይወት ወደ ሀገራቸው ከሚመለሱት ባለፈ በየመንገዱና ማኅበራዊ ሚዲያ የሚሰሙትም ነገሮች አሳዛኝና አስፈሪም ናቸው። እኛም ለዛሬው ዝግጅታችን በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና የተመላሽ ዜጎች ድጋፍና ክትትል መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ደረጀ ተግይበሉ አነጋግረን የሚከተለውን አካፍለውናል።

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ የሰዎች ዝውውርን ሕገ ወጥና ሕጋዊ የሚያሰኘው ምንድን ነው?**

**አቶ ደረጀ፤** የሰዎች ዝውውር የሚባለው በዋናነት አንድ ሀገር ያወጣውን ሕግ ወይንም ደግሞ ሌሎች ዓለም አቀፍ ሕጎች በመጣስ የዛን ሀገር ድንበር ጥሶ መግባት ማለት ነው። ሕገ ወጥ ስደት የሚባለው መደበኛ የሆነ ፍልሰት እና መደበኛ ያልሆነ ፍልሰት ተብሎም ይለያል፡፡ ይህ የሚባለው ከስደተኞቹ መካከል ተገደውም የሚሄዱ በመኖራቸው ነው። መደበኛ ያልሆነ ፍልሰት የሚባለው መዳረሻ ወይንም መተላለፊያ የሆነው ሀገር ያወጣውን ሕግ ጥሰው፤ አልያም ደግሞ ወደ ሀገር ውስጥ ለመግባት ያስቀመጠውን ሕግና መስፈርት እንዲሁም መረጃ ሳያሟሉ መግባት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሕገ ወጥ ስደት እንዲፈጸም የሚያደርጉት እነማን ናቸው? ድርሻቸውስ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ደረጀ፤** ይሄ ሲፈጸም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ይኖራሉ። ከእነዚህም መካከል ሰዎቹን የሚያቀባብሉ ሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች/ደላሎች እና በሕገወጥ መንገድ ሰዎቹን ድንበር የሚያሻግሩ አካላትንም ያካትታል ።

እነዚህ አካላት ዓላማቸው የተለያየ ነው። ሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች/ደላሎች ዓላማቸው ብዝበዛን መሠረት ያደረገ ነው። በዚህም የገንዘብ ዝርፊያን እና ስደተኞቹን እንደ ባርያ የጉልበት ብዝበዛ ማድረግን፤ የግዳጅ ጋብቻ መፈጸምን፤ እንዲሁም ወጣትና ሕጻናት ሴቶችን ለሴተኛ አዳሪነት በማድረግ የገቢ ምንጭ ማግኛ ማድረግን ያካትታል። በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ከስደተኞቹ ላይ የተለያዩ የሰውነት ክፍላቸውን አካል እስከመውሰድ የሚደርሱ ናቸው። በዚህ መካከል የሚፈጸሙ ጥቃቶች ስደተኞቹን እስከሞት የሚያደርሱም ናቸው። በሌላ በኩል በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር የሚያሻግሩ አካላት የሚባሉት የተለያዩ ወንጀልና ጥፋቶችን የሚፈጽሙ ቢሆንም ዓላማቸው ገንዘብ ማግኘትን ብቻ መሠረት ያደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- በሕገወጥ መንገድ ከሀገር የሚወጡ ዜጎች የሚደርስባቸው ችግር እንዴት ይታያል ?**

**አቶ ደረጀ፡-** በሕገወጥ መንገድ ከሀገር የሚወጡ ዜጎች ድንበር ከተሻገሩበት ጊዜ አንስቶ ለተለያዩ ችግሮች መዳረግ ይጀምራሉ። ከእነዚህም ውስጥ በስፋት የሚታወቁት ለአካላዊ መጎሳቆል ከውሃ ጥም ጀምሮ የምግብና መጠጥ እጦት ይህንን ተከትሎና በሌሎች ምክንያቶች ለበሽታና ለሞት የሚጋለጡበት አጋጣሚም ይፈጠራል። በዚህ ሁኔታ በምድር የሚያደርጉትን ጉዞ ካጠናቀቁ ሌላውና ዋናው ፈተና የሚገጥማቸው ባሕር ሲያቋርጡ ነው። በዚህ ወቅትም ሁሉም ሊባል በሚችል ደረጃ የሚሳፈሩባቸው ጀልባዎች ደረጃቸውን የጠበቁ አይደሉም። ከዚህም ባለፈ ከአቅም በላይ ስደተኞችን ስለሚያሳፍሩ በተደጋገሚ የምንሰማው የጀልባ መገልበጥና መስጠም ይከሰታል።

**በሕገወጥ መንገድ ከሀገር የሚወጡ ዜጎች ድንበር ከተሻገሩበት ጊዜ አንስቶ ለተለያዩ ችግሮች መዳረግ ይጀምራሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በስፋት የሚታወቁት ለአካላዊ መጎሳቆል ከውሃ ጥም ጀምሮ የምግብና መጠጥ እጦት ይህንን ተከትሎና በሌሎች ምክንያቶች ለበሽታና ለሞት የሚጋለጡበት አጋጣሚም ይፈጠራል**



አቶ ደረጀ ተግይበሉ

በተጨማሪ ሕገወጥ አዘዋዋሪዎቹ ወደ ዳር ከተጠጉ ልንያዝና ችግር ሊገጥመን ይችላል በሚል ስጋት ወደ ድንበር ሳይጠጉ ስደተኞቹን ያወርዷቸውና ዋና የማይችሉት ሕይወታቸውን ለማጣት ይጋለጣሉ። በዚህ ረገድ በቅርቡ በጅቡቲ የተፈጠረውን ተመሳሳይ አሳዛኝ አጋጣሚ ማስታወስ ይቻላል። እነዚህ ስደተኞች ለአደጋ የተጋለጡት ወደ ሌላ ሀገር እየሄዱ አልነበረም። በነበሩበት ቦታ ምቹ ሁኔታ ስላልገጠማቸው ችግሩ አስመርሯቸው ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ወስነው ባደረጉት ጉዞ ነው። ሕገወጦቹ አዘዋዋሪዎች ባሕሩን በሠላም ቢሻገሩም ድንበር እንደተጠጉ መሬት ሳይደርሱ ስላወረዷቸው ዋና የማይችሉት ሕይወታቸውን ለማጣት በቅተዋል። በባሕር የሚሄዱት ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች አልፈው ባሕር አቋርጠው መሬት ለመርገጥ ዕድሉን ቢያገኙም ለመተላለፊያ በሚያቋርጧቸው ሀገራትም የሚደርስ በርካታ ሰቃይ ይጠብቃቸዋል።

ለምሳሌ በጅቡቲ የሚንቀሳቀሱ ስደተኞች ባሕር አቋርጠው የሚያርፉት የመን ነው። የመኖች ደግሞ በአሁኑ ወቅት በርስ በርስ ግጭት ውስጥ ያሉ ሕዝቦች ናቸው። በተጨማሪ እንደ ሀገርም ከጎረቤት ሀገራት ጋር ጦርነት አለባቸው። በዚህም የተነሳ አብዛኞዎቹ ስደተኞች ልጆችና ወጣቶች በመሆናቸው ለሽብር፤ ለውትድርና እና ሌሎች እኩይ ተግባራት የሚመለመሉበት አጋጣሚም ሰፊ ነው። አንዳንዶቹ ቡድኖችም ልጆቹን የየራሳቸው አገልጋይ አድርገው የሚያስቀሯቸው ሲሆን በመርከብ ላይ ለሚሠሩ ወንጀሎችና የሽብር ተግባራት የሚያሳትፏቸውም አሉ።

ይህንንም አልፈው በዛ አካባቢ መዳረሻ ተደርጋ ወደምትታሰበው ሳዑዲ ሲደርሱ የድንበር ጠባቂ ወታደሮች በጥይት እስከ መምታት የሚደርስ እርምጃ ይወስዱባቸዋል። በዚህ አይነት ለስደት ከተንቀሳቀሱት ዜጎች መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከላይ በተዘረዘሩትና ተመሳሳይ ችግሮች የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራትንም ሆነ አውሮፓን ሳይረግጡ ከመንገድ የሚቀሩ ይሆናል። በተመሳሳይ ችግር ወስጥ በመተማ በሱዳን በኩል እንዲሁም በደቡብ ክልል በኬንያ በኩል የሚሰደዱት በርካቶች ናቸው።

ይህ እውነት የየእለት ዜና መሆን ከጀመረ ሰነባብቷል። በአሁኑ ወቅት እንደአዲስ እየተስፋፋ የመጣው ደግሞ ስደተኞቹ ላይ ከሚያደርሱት ጉዳት እንግልትና ገደላ ባለፈ አስገድደው ከቤተሰብ ገንዘብ የሚያስልኩም መበርከታቸው ነው። ብዙ ልጆች በግለሰቦች እየታገቱ ሲሆን ቤተሰብ ለማስመለስ ገንዘብ ይጠየቃል። ደላሎቹ የሚጠይቁትን ገንዘብ አግኝተውም አንዳንዶቹን የላኩበትን መስመር ተከተለው የሚመልሷቸው ሲሆን አንዳንዶቹ ግን ብሩም ተበልቶ የውሃ ሽታ ሆነው ይቀራሉ። ይህ የስደተኞቹን ቤተሰቦች ለተደጋጋሚ የኢኮኖሚ ጉዳትና ለከፍተኛ ጭንቀት የሚዳርግ ነው።

ከዚህ ሁሉ እንግልት ባለፈም በሕገ ወጥ መንገድ ሲንቀሳቀሱ በመያዛቸው ለረዥም ዓመታት በእስር የሚያሳልፉትም ብዙዎች ናቸው። በዚህ ረገድ በታንዛንያ ዛሬም ድረስ በርካታ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን አይደለም ወደ ፈለጉበት ሀገር ሊደርሱ ወደ ሀገራቸውም መመለስ ሳይችሉ አዛው ይገኛሉ። በተመሳሳይ ዛምቢያ ሞዛምቢክና ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ውስጥም አሉ ።

**አዲስ ዘመን፡- ዜጎች ከሀገር ወጥተው ስመሥራት በሕገወጥ መንገድ በደላሎች ስመንቀሳቀስ የሚወስኑት ስምንድን ነው ?**

**አቶ ደረጀ፤** ዜጎች ሕገወጡን መንገድ መርጠው ለእነዚህ አስከፊ ችግሮች ሊዳረጉ የሚችሉት ደላሎቹ ለጥቅማቸው ሲሉ ቀድመው በሚያደርሷቸው የተሳሳተ መረጃ በመታለል ነው። የሚያታልሏቸውም የሚስብ አማላይ ነገሮችን በመንገርና ሊፈጸም የማይችል ተስፋ በመስጠት ነው። በሕገ ወጥ መንገድ የሄዱ ዜጎች ሁሌም ለጉዳት ተጋላጭ ናቸው። በለስ ቀንቷቸው የፈለጉበት ቦታ ቢደርሱ እንኳን በሕጋዊ መንገድ እንደሚሄዱት ሌሎቹ ተጓዦች መብታቸውን ማስከበር የሚችሉበት ዕድል አይኖርም። አንዳች ጉዳትና ችግር ቢገጥማቸው እንኳን በመንግሥትም ሆነ በሌሎች አካላት እርዳታ ለማድረግ ቢፈለግ ያሉበት ቦታ ስለማይታወቅ ሁሉም ነገር አስቸጋሪ ይሆናል። ያሉበት ቦታ ከታወቀ አዘዋዋሪዎቹም ሆኑ ደላሎቹ ተጠያቂ ስለሚሆኑ የሚያቆዩዋቸው በድብቅ ቦታ ነው። በዚህ ሁኔታ ቆይተው ሲመለሱ ብዙዎቹ ከሥነ ልቦና መቃወስ ጀምሮ በርካታ ችግሮች ይዘው ነው። በተለይም ሴቶቹ በተደጋጋሚ በሚደርስባቸው ፆታዊ ጥቃት አርግዘው የሚመጡ ሲሆን አብዛኛዎቹ ከማን እንደፀነሱ እንኳን ማወቅ አይችሉም። ስደተኞቹ ከሀገር ሲወጡ መሬትን ጨምሮ ንብረት አስይዘው ከአበዳሪ ተቋማት ተበድረው ወይንም የቤተሰብ ጥሪት የሚሆኑ ከብቶችን አሽጠው ነው። ተይዘው ሲመለሱ ግን ነጠላ ጫማ እንኳን ሳይዙ ነው። እነዚህ ችግሮች ዘላቂ ጉዳትና ጸጸት የሚያስከትሉ ናቸው።

ወጣቶቹ ተታለው የሚሄዱት በመንግሥት ከሚደርሳቸው መረጃ በላይ አጠገባቸው ያሉ ደላሎችን ስለሚያምኑ ነው። በተለይም ደላሎቹ ከዚህ በፊት ሰው ልከው የሚያውቁ ከሆነ የመታመን ዕድላቸው ሰፊ ነው። ከዚህም ባለፈ እኛ ቶሎ እንጨርስላችኋለን የመንግሥት ይቆያል የሚል የተሳሳተ መረጃ የሚሰጧቸው ሲሆን ሊገጥማቸው ስለሚችለው ችግር ግን የሚነግሯቸው ነገር አይኖርም። አብዛኞቹ ደላሎች ደግሞ በሚኖሩበት አካባቢ የተሻለ ተደማጭነትና ያቃሉ ተብለው የሚታሰቡ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ በዚህ ተግባር ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው ወደ ውጪ የሚልኩ ኤጀንሲዎችም ሲሳተፉበት ይታያል። በዚህ ላይ ለስደት የሚነሱ ወጣቶች በገጠር አካባቢ የሚኖሩ በመሆናቸው ስለ ሕገወጥና ሕጋዊ ስደት ትክክለኛ ግንዛቤ ያላቸውን ሰዎች የማግኘትና በመደበኛውም ሆነ በማኅበራዊ ሚዲያ መረጃ የማግኘት እድላቸው ጠባብ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መደበኛ ስደተኞች የሚባሉት እነማን ናቸው? በመደበኛነት የሚደረግ ጉዞስ የሚያስገኘው ጠቀሜታ ምንድን ነው ?**

**አቶ ደረጀ፤** መደበኛ ስደተኞች የሚባሉት በሕጋዊ መንገድ መንግሥት አውቋቸው በታወቁና ለዚህ ተብለው በተዘጋጁ ቦታዎች ሥልጠና ወስደው ወደሌሎች ሀገራት ለሥራ የሚሄዱትን ነው። በሕጋዊ መንገድ መሄድ በጉዞ ወቅት ከሚደርስ እንግልትና ስቃይ ከመዳን ባለፈ መብትና ጥቅሞቻቸው ቀደመው የታወቁ በመሆናቸው ተረጋግተው እንዲቆዩ ይረዳል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ቀጣሪዎቻቸው የሚታወቁ በመሆኑም ጉዳት ከደረሰ በወቅቱ ለመከላከል እንዲሁም ገንዘባቸውን ከተከለከሉ እና የጉልበት ብዝበዛ ከተካሄደባቸው በቀላሉ መጠየቅ ይቻላል። በዚህ ረገድ ለሚከሰቱ ችግሮች ሀገር ቤት የላካቸው ኤጀንሲ በመኖሩ ጉዳዩንም ለመከታተል በጣም

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ወቅታዊ

# ሕገ ወጥ ስደትና...

ከገጽ 9 የዞረ

ቀላል ይሆናል።

ለምሳሌ ሠራተኞቹ የሠሩበትን ክፍያ ቢከለከሉ ኤጀንሲዎች እዚህ ሆነው የሚከፍሉት ገንዘብ እንደዋስትና ያስይዛሉ። ነገር ግን በዚህ ረገድ እንደሚባለው የከፋ ችግሮች የሉም፡፡ ይህም ሆኖ ለኤምባሲ ያሳወቁና ችግሩ የተፈታላቸው በርካቶች አሉ። በቀጣይ አሠራሮችን ለማስተካከል የሚሠሩ ሥራዎችም ይኖራሉ። ከዚህም ውስጥ በሕጉ ላይ «ሌበር አታሼ» በየሀገራቱ እንደሚቀመጥ የተወሰነ በመሆኑ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሠራ ይሆናል። እነዚህም ለሀገሪቷ ወኪል ሆነው የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነቱን የሚከታተሉ በኤምባሲዎች የሚመደቡ ይሆናል። እነዚህ ባለሙያዎች የሠራተኞች መብት ከተጣሰ ስምምነቱን መሠረት በማድረግ ለማስከበር ይሠራሉ።

ዜጎች ይህንን በመረዳት በምንም መልኩ ወደ ደላሎች መሄድ አይኖርባቸውም። በአሁኑ ወቅት በመንግሥት በኩል ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል እታች ደረስ ወርደው በሴቶች አደረጃጀት በኩል እየሠሩ ይገኛል። ይህም ሆኖ ከችግሩ ስፋት እና ካለው ድህነት አንጻር አሁንም ድረስ በሕገወጥ መንገድ የሚሄዱ ወጣቶች አሉ። ለዚህ በዘላቂነት መፍትሔ የሚሆነው የሥራ ዕድል በመፍጠር ዜጎች በሀገራቸው ሠርተው የሚለወጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በሕጋዊ መንገድ የሚደረጉ የጉዞ ዝግጅቶችን አስመልክቶ ኅብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረው እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች በቂ ናቸው ሲባል ይችሳል ?**

**አቶ ደረጀ፤** የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራው በተለያዩ አካላት በስፋት እየተሠራበት ይገኛል። በተለይም የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይን የሚመለከቱ ቢሮዎች ተቀዳሚ ሥራቸው ይሄ ነው። በአንዳንድ ክልሎች ደግሞ አደረጃጀታቸው የሥራና ክህሎትን የሚመለከት ሲሆን የአንድ ማዕከል የሚል አገልግሎት ተከፍቶ እየተሠራ ይገኛል። በእነዚህ ቢሮዎችም መረጃዎች ሥልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ ወረዳ ድረስ እየተሄደ ይሠራል። እነዚህ አካላት ከመንግሥት ተቋማትና የሰው ኃይል ባለፈ በሴቶች ጉዳይ ላይ የሚሠሩ አደረጃጀቶችንም ይጠቀማል።

ነገር ግን ተቀባይነት በማግኘት ረገድ ወጣቶቹ ቅድሚያና ትኩረት ሰጥተው መረጃውን አምነው የሚቀበሉትና ለተሳሳተ ውሳኔ የሚዳረጉት በቅርባቸው ካሉ ደላሎች ነው። አንዳንዶቹ ካሉበት መንደር ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ጀምሮ ክፍያ ሲሰጡ ስለሚቆዩ መጨረሻ ፌዴራል ደረጃ ሲደርሱ ሰማኒያ ሺህ ሰባ ሺህ አውጥተናል ይላሉ። በርካቶች ደግሞ የከፈሏቸውን ሰዎች በቅጡ ስለማያውቋቸውና አድራሻም ስለማይዙ ገንዘባቸው አየር ላይ ተበልቶ ይቀራል። አንዳንዶቹ ገንዘቡን የሚከፍሉት የራሴ የሚሏቸው ሰዎች እጅ ስለሚኖርበትም ዕድሉን አግኝተው ክስ ሲመሠረትም በቂ መረጃ የማይሰጡ አሉ። ይህም ወንጀል ተፈጽሞ ጉዳዩ ወደሕግ ቢቀርብ እንኳን ውጤታማ እንዳይሆን እንቅፋት ይፈጥራል።

**አዲስ ዘመን፡- ሕገ ወጥ ስደት ከግለሰብና ከቤተሰብ ባለፈ እንደ ሀገር የሚያስከትለው ተፅዕኖ እንዴት ይታያል?**

**አቶ ደረጀ፤** ሕገ ወጥ ስደት በሀገር ላይ የሚያደርሰው ጉዳትም ቀላል አይደለም። አብዛኞዎቹ የሚሰደዱት ወጣቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ወጣቶች ከፍተኛ የሀገር ሀብት ፈሶባቸው የተማሩ ናቸው። እነሱም ለስደት የሚዳረጉት ያላቸውን አቅም በመጠቀም ራሳቸውን፤ ቤተሰባቸውንና ሀገራቸውን ለመጥቀም በማሰብ ነው። በእርግጥም አካሄዳቸው በሕጋዊ መንገድ ቢሆን እንደ ሀሳባቸው እነሱም ቤተሰብም ማኅበረሰብና ሀገርም መጥቀም ይችላሉ። በአሁኑ ወቅት በርካታ ሀገራት ከውጪ ወደሀገር ውስጥ በሚላክ ገንዘብ ከውጪ ምንዛሪ ጀምሮ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ሲሆኑ ይታያል።

ከዚህ በተጨማሪም ዜጎች በተለያዩ መንገዶች ከሀገራቸው ውጪ ወጥተው በሌሎች ሀገራት ሲቆዩ የሚያገኟቸው ጠቃሚ የሆኑ ልምዶች፤ እውቀቶች፤ ቴክኖሎጂና ጠንካራ የሥራ ልምዶችም ይኖራሉ። በአሁኑ ወቅት ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ ይዘው በመምጣት በሀገራቸው ኢንቨስት በማድረግ ብዙዎችን ተጠቃሚ ሲያደርጉ እያየን ነው። ነገር ግን ይህ ሁሉ ሊሆን የሚችለው በሕጋዊ መንገድ መንቀሳቀስ ሲቻል ነው። በአሁኑ ወቅት ግን አብዛኞዎቹ ከሀገራቸው እየወጡ ያሉት ሕጋዊ መንገድን ተከትለው ባለመሆኑ እነዚህን ዕድሎች ማግኘት አይችሉም። ይልቁን እዛው እያሉም በሚገባቸው ደረጃ ተጠቃሚ አይሆኑም፡፡ ይብስ ብሎ አንዳንዶቹ ለራሳቸውም ብሎም ለሀገርና ለቤተሰብ የሚተርፍ ዕዳ እና ስቃይ ይዘው ይመለሳሉ።



**በአሁኑ ወቅት የሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገራት የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በምሥራቁ የሀገሪቱ ክፍል በጅቡቲ በር ብቻ በየዓመቱ ከአንድ መቶ ሀምሳ ሺ እስከ ሁለት መቶ ሺ የሚደርሱ ዜጎቸ በሕገወጥ መንገድ ከሀገር ይሰደዳሉ**

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ሀገር ሕገ ወጥ ፍልሰትን ስመከላከልና ስመቆጣጠር የሚያስችል የሕገ ማዕቀፍና አሠራር አለ ስማለት ይቻላል?**

**አቶ ደረጀ፡-** በኢትዮጵያ በዚህ ረገድ የተዘጋጁትና እየተተገበሩ ያሉት ሕጎች ችግር የለባቸውም። አንዳንድ ክፍተቶች ሲኖሩም በየወቅቱ የእርምት ማስተካከያ እየተደረገላቸው የሚሠሩ ናቸው። በዚህ ረገድ መንግሥት መሥራት ያለበትን ሥራ በአግባቡ እየሠራ ይገኛል። ይህም ሆኖ ዘርፉ ከፍተኛ ገንዘብ የሚንቀሳቀስበትና ጥቅም የሚያስገኝም በመሆኑ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮች እንደሚኖሩ ይገመታል። ይህ አይነት ችግር በሌሎች መስኮችም ሊከሰት የሚችል ነው። በአሁኑ ወቅት አብዛኛውን አሠራር በቴክኖሎጂ ለመምራት የተጀመሩት ሥራዎችም እንደ ደላሎችና ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠርና በወቅቱ እርምጃ ለመውሰድ በማሰብ ነው። ይህም በሕገወጥ መንገድ የሚከናወኑ ተግባራትን በመግታት የዜጎችን መብትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ይሆናል። በተጨማሪ መንግሥት ይህንን የጀመረው በስሩ በአስፈጻሚው አካል በኩል ያለ የአገልግሎት አሰጣጥንም ሆነ ኤጀንሲዎችን ለመቆጣጠር ሁኔታዎችን የሚያመቻች በመሆኑ ነው።

ይህም ሆኖ ዛሬም ድረስ በሞባይል ስልክ መልእክት በመላክና በሌሎች መንገዶችም በሕጋዊ መንገድ ወደውጪ ሀገር የሥራ ስምሪት አገልግሎት ለማግኘት ምንም ክፍያ እንደሌለ ቢነገርም እያታለሉ የሚቀበሉ ወንጀለኞች ግን አሉ። ለምሳሌ በኦን ላይን የሲ ኦ ሲና ሌሎች መረጃዎችን ለመጫን በሺዎች የሚቆጠር ገንዘብ የሚጠይቁ አሉ። ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ሲያጭበረብሩ የተያዙና ሕጋዊ እርምጃ የተወሰደባቸው ያሉ ሲሆን ለቀጣይም ኅብረተሰቡ ይህን የሚያደርጉ አካላትን ሲመለከት ያገባኛል በሚል መጠቆም ይጠበቅበታል ።

**አዲስ ዘመን፡- አብዛኞቹ ሕገወጥ ስደተኞች ከሀገር የሚወጡት በደንበር በኩል የጎረቤት ሀገራትን አቋርጠው መሆኑ ይታወቃል። መንግሥት ችግሩን ስመቅረፍ ከእነዚህ ሀገራት ጋር የሚሠራቸው ሥራዎች አሉ ?**

**አቶ ደረጀ፤** በመንግሥት በኩል ችግሩን በመቅረፍ የዜጎችን መብትና ጥቅም ያስከብራሉ የሚላቸውን ሥራዎች በሙሉ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ በቀጣይም አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። በዚህ ረገድ ከጎረቤት ሀገራት ጋር በተያየዘ ያለውን ግንኙነት ውጤታማ ለማድረግ የድንበር አስተዳደርን በተመለከተ በተለያዩ ጊዜያቶች የተደረጉና ወደፊትም የሚደረጉ ውይይቶች አሉ። በተጨማሪ በዚህ ጉዳይ ተሳታፊ የሆኑ ወንጀለኞችን በሕግ ተጠያቂ ለማድረግ አሳልፎ በመስጠት ረገድም የሚደረጉ ስምምነቶችም አሉ። በቅርቡ ከጅቡቲ መንግሥት ጋር ውይይት ተካሂዷል። በርካታ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችም በተለያዩ ጊዜያት ይካሄዳሉ። የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ደግሞ በተለየ ከፍተኛ ፍልሰት የሚታይበት በመሆኑ ለፍልሰተኞች ጉዳይ ምላሽ የሚሰጥ የአምስት አመት እቅድ በመያዝ እየተሠራ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ዛሬ ላይ ምን ያህል ስደተኞች በሕገ ወጥ መንገድ ከሀገር ይወጣሉ ተብሎ ይገመታል ?**

**አቶ ደረጀ፤** በአሁኑ ወቅት የሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገራት የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በምሥራቁ የሀገሪቱ ክፍል በጅቡቲ በር ብቻ በየዓመቱ ከአንድ መቶ ሀምሳ ሺ እስከ ሁለት መቶ ሺ የሚደርሱ ዜጎች በሕገወጥ መንገድ ከሀገር ይሰደዳሉ። በመተማ በኩል ወደሱዳንና በደቡብ በኬንያ ደግሞ ቁጥራቸው በዚህ ደረጃ ባይሆንም የሚሰደዱም አሉ። በሕገወጥ መንገድ ከሀገር የሚሰደዱ ዜጎች መዳረሻም እየጨመረ ነው። ለምሳሌ እስከ ቅርብ ጊዜ ስደት ሲታሰብ ማይናማር የምትባልን ሀገር የሚያስብ አልነበረም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ታይላንድ ትሄዳላችሁ ተብለው ደላሎች አታለው መዳረሻቸውን ማይናማር ያደረጉባቸው አሉ። ወደነዚህ ሀገራት የሚወስዷቸው ደግሞ በተለየ መልኩ የተማሩ የሠለጠኑ የሚባሉትን ነው። የሕገወጥ ስደተኞች ቁጥር የተጋነነ ስለመሆኑ የጀልባ መገልበጥን ጨምሮ በተለያዩ አደጋዎች በመንገድ ከሚቀሩትና በለስ ቀንቷቸው ያሰቡበት ደርሰው ሥራ ከጀመሩት ባለፈ በየወቅቱ ወደሀገረ ቤት የሚመለሱት አመላካች ነው ።

በዚህ ረገድ ባለው ባለፈው አንድ ዓመት ብቻ ማለትም ከጥቅምት አራት ሁለት ሺህ አስራ ስድስት እስከ ሁለት ሺህ አስራ ሰባት መስከረም ማጠናቀቂያ አንድ መቶ አርባ አምስት ሺህ ሦስት መቶ ሠላሳ ዜጎች ወደሀገራቸው ተመልሰዋል። እነዚህ ከተለያዩ ሀገራት የመጡ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት ከሳዑዲ የመጡ ናቸው፡፡ ከሳዑዲ የመጡት ብቻ ዘጠና አንድ ሺ ስድስት መቶ አርባ ሁለት ናቸው። ከየመን ሦስት ሺ ስድስት መቶ አስራ ስድስት፤ ከኦማን ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ሃያ ስድስት ከሱዳንም የተከሰተውን የርስ በርስ ጦርነት ተከትሎ አርባ ሰባት ሺ ሰባት መቶ አርባ ስድስት ናቸው። ይህን መነሻ አድርጎ በርካታ የተያዙ እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል። በየሀገራቱ ያልተያዙ በየእስር ቤቱ ያሉትንም ማሰብ ይቻላል።

አብዛኞቹ ከአስራ አምስት እስከ ሠላሳ አምስት ዓመት እድሜ ያላቸውና አምራች ወጣቶች ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ የተማሩና በተለያየ ዘርፍ የሠለጠኑም ይገኙበታል። ይህም ሆኖ ከመጡ በኋላ በቀጥታ ሥራ እንዳይጀምሩና ራሳቸውንን ሀገራቸውን እንዳይጠቅሙም ተመላሾቹ አንዳንዶቹ የአካል አብዛኞቹ ደግሞ የአእምሮ መታወክን ጨምሮ የሥነ ልቦና ጉዳት የደረሰባቸው ናቸው። ይህም በመሆኑ በቤተሰብ በመንግሥትና በሌሎች ተቋማት በኩል ቀዳሚ ሥራ የሚደረገው የእነሱን ጤና መመለስ ላይ ነው።

በመሆኑም ይህንን ሕገ ወጥ ተግባር ለመከላከልም ግንዛቤ ከመፍጠር ጀምሮ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛል። በቀጣይም ችግሩን ለመከላከል ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትና ሌሎች ድርጅቶች ጋር የተጀመሩት ሥራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናል። ይህም ሆኖ ሕገወጥ የሰዎች ፍልሰትን ለመቆጣጠር ኅብረተሰቡ ጉዳዩ ይመለከተኛል በሚል በንቃት ሊሳተፍበት ይገባል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ወጣቶችም በተሳሳተ መረጃ ባለመታለል እራሳቸውን ከሕገወጥ ስደትና ያንን ተከትሎ ከሚከሰቱ ተደራራቢ ችግሮች ሊጠብቁ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ጊዜ እናመሰግናለን ፤**

**አቶ ደረጀ፤** እኔም አመሰግናለሁ።

# ፋሽን

## ኢትዮጵያ የተሳተፈችበት የሞስኮው የብሪክስ የፋሽን መድረክ

**ሰሚራ በርሀ**

በኢኮኖሚያቸው በከፍተኛ ደረጃ እያደጉ ያሉት ብራዚል፣ ሩሲያ፣ ቻይና፣ ሕንድና ደቡብ አፍሪካ ትብብራቸውን ልማታቸውንና ደኅንነታቸውን የሚያጠናክርላቸውን ብሪክስ የተሰኘ ተቋም ከመሠረቱ ዓመታት ተቆጥረዋል። እነዚህ ሀገሮች በቅርቡ ደግሞ ኢትዮጵያን፣ ግብፅን፣ የተባበሩት ዓረብ ኤምሬትን ጨምሮ ሌሎች ሀገሮችን በአባልነት ይዘዋል።

ጥምረቱ ሀገሮቹ ኢኮኖሚያቸውን የሚያሳድጉበት፣ ለምርቶቻቸው ገበያ ለመክፈትና ለማፈላለግ በትብብር የሚሠሩበት፣ በአጠቃላይ የገበያ ትስስራቸውን የሚያስፋፉበት የትብብር መድረክ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። በማኅበራዊ ዘርፎችም እንዲሁ በጤናና በትምህርት እንዲሁም በሳይንስና ቴክኖሎጂም ጭምር ትስስር በመፍጠር ልማታቸውን የሚያሳልጡበትም እንደሚሆን ይጠበቃል።

በያዝነው የፈረንጆቹ ዓመት 2024 በጥር ወር ኢትዮጵያም የዚህ ጥምረት አባል መሆኗ ይታወሳል። ኢትዮጵያ የዚህ ጥምረት አባል መሆኗ ከጥምረቱ መሥራቾች ጋር ብቻ ሳይሆን አባላት ጋርም በተለይ በምጣኔ ሀብት ረገድ የሚኖራትን ትስስር ይበልጥ እንደሚያጠናክርላት ይታመናል።

በተለያዩ የምጣኔ ሀብቱ ዘርፎች ግንኙነትን ለማጠናከር የሚያስችለው የዚህ ጥምረት መሥራቾችና በፋሽን ኢንዱስትሪያቸውም ቀላል የማይባል ገንዘብ የሚዘዋወርባቸው ናቸው። በዚህም ባሕልን፣ ማንነትን ለመግለጽ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዳለውም ይታሰባል። ይህንን ሀሳብ ለማጎልበት እና የጥምረቱ አባል ሀገራት በዘርፉ ላይ ያላቸው እንቅስቃሴ ውጥነትን የተከተለ እንዲሆን የሚያስችል መድረክ በቅርቡ ተካሂዷል ።

መድረኩን አስመልክቶ የወጣ መረጃ እንዳመለከተው፤ ይህ ብሪክስ የፋሽን የተሰኘ መድረክ በሞስኮ ባሳለፍነው




ሳምንት እ.አ.አ ከጥቅምት ሦስት እስከ አምስት ለሦስት ቀናት ነው የተካሄደው። በዓለም አቀፍ ደረጃ እወቅና ካላቸው የፓሪስ ፋሽን ሳምንት እንዲሁም የሚላን ፋሽን ሳምንት ተከትሎ የተካሄደው ትልቅ የፋሽን መድረክ መሆኑ ተነግሮለታል። ከ100 በላይ የሚሆኑ ከተለያዩ ሀገራት የተወጣጡ ተሳታፊዎች እንደተገኙበት የተጠቆመ ሲሆን፣ ይህም ብሪክስ በፋሽን ኢንዱስትሪው ላይ እያሳየ ያለው ተፅዕኖ የተንጸባረቀበት ተብሏል።

በመድረኩም በፋሽን ኢንዱስትሪው እየታየ ስላለው ለውጥ ውይይት ተካሂዷል። በዚህ መድረክ ላይ በየዓመቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚዘጋጀው የ‹‹ሀብ አፍ አፍሪካ ፋሽን ሳምንት›› መሥራች እና አዘጋጅ የሆነችው ማሕሌት ተክለማርያም ኢትዮጵያን ወክላ ተሳትፋለች ።

በወቅቱም ‹‹የብሪክስ ዓለምአቀፍ የፋሽን ፌዴሬሽን›› ይፋ ተደርጓል። ፌዴሬሽኑ በአባል ሀገራት የሚገኙ የፋሽን ፈጠራዎችን በአንድ በማምጣት፣ የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦችን እና ልዩ ልዩ ባሕላዊ መግለጫዎችን የሚያቀርብ እና አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦችን እና ፈጠራዎችን ለዓለም አቀፍ ፋሽን ኢንዱስትሪ የሚያስተዋውቅ መሆኑም ተገልጿል።

የፌዴሬሽኑ መመሥረት ዋና ዓላማም በአባል ሀገራቱ በተለያዩ የፋሽን ዘርፎች ላይ የተሠማሩ ኢንዱስትሪዎችን ማጠናከር፣ የተለያየ ችሎታ እና ተሰጥዖ ያላቸውን ዲዛይነሮች መደገፍ፣ የባሕል ልውውጥን ማበረታታት፣ የጋራ የሆነ የግብይት መስመርን መፍጠር ነው ተብሏል ።

የሞስኮ ምክትል ከንቲባ ናታሊያ ሰርጉኒና የብሪክስ ዓለም አቀፍ የፋሽን ፌዴሬሽን መመሥረት ለብሪክስ ትልቅ ስኬት መሆኑን አስታውቀዋል። የፋሽን ኢንዱስትሪ ፌዴሬሽን መመሥረት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሳታፊ ለሆኑት ሀገራት ቁልፍ ጉዳይ የሚጋሩበት መድረክ ሊሆን እንደሚችልም ገልጸዋል።

በመድረኩ ላይ ከበርካታ ሀገራት የተውጣጡ በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ላይ የሚሠሩ፣ የፋሽን ሳምንት አዘጋጆች እንዲሁም የፋሽን ትምህርት ቤት ባለቤቶች፣ ዲዛይነሮች ተገኝተዋል። በብሪክስ ዓለምአቀፍ የፋሽን ፌዴሬሽን አባል ከሆኑት ሀገራት መካከልም ኢትዮጵያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ግብፅ፣ ስፔን፣ አሜሪካ፣ ኢንዶኔዢያ፣ ማሌዢያ፣ ጋና፣ ኬንያ፣ ታንዛኒያ ይገኙበታል።

ኢትዮጵያን ወክላ በመድረኩ የተገኘችው የሀብ አፍ አፍሪካ ፋሽን ሳምንት መሥራች እና አዘጋጅ ማሕሌት ተክለማርያም በመድረኩ ላይ ንግግር አድርጋለች። መድረኩን አስመልክተን ያነጋገርናት ማሕሌት ዝግጅቱ በፋሽን ኢንዱስትሪው ከሚሠሩ ዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ጋር ለመገናኘት እና ትውውቅ ለመፍጠር ትልቅ ዕድል መሆኑን ገልጻለች።

‹‹ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል ሀገር እንደመሆኗ በዚህ ዓለም አቀፍ የፋሽን ፌዴሬሽን ላይም አባል ሆናለች። ፌዴሬሽኑ በፋሽን ኢንዱስትሪው ላይ የተማሩ ባለሙያዎችም ሆኑ ነጋዴዎች ከሌሎች ሀገራት አቻዎቻቸው ጋር ያላቸውን የገበያ ትስስር በእጅጉ እንዲያሳድጉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በሀገራችን በመነቃቃት ላይ ለሚገኘው የፋሽን ዘርፍ እድገትም የራሱ የሆነ ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖረዋል›› ስትል ገልጻለች።

የብሪክስ ዓለም አቀፍ የፋሽን ፌዴሬሽን መቋቋም በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ ራዕይ ያላቸውን የፋሽን ኢንዱስትሪው የፈጠራ ባለቤቶች ሥራዎቻቸውን በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲያሳዩ እና እውቅና እንዲያገኙ ከመሥራት ባሻገር የፋሽን ኢንዱስትሪው በሚኖረው የአመራረት ሒደት በተፈጥሮ ላይ እንዲሁም በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚያመጣው አሉታዊ የሆነ ተፅዕኖን በመቀነስ ረገድም የራሱን ሚና ሊጫወት እንደሚችል በመድረኩ ላይ ተገልጿል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ‹‹ እንኳንም ቀረብሽ ... ››

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

መቼም ዘንድሮ ይህ ማኅበራዊ ሚዲያ ይሉት ጉዳይ አያሳየን የለም። ሰሞኑን ከአንዲት ወዳጄ ገጽ ደርሶ ያየሁት አንድ ወሬ በእጅጉ ሲያስደንቀኝ ከረመ። ነገሩ እንዲህ ነው። አንድ ከፍ ያለ ባለ ክሬም ኬክ ዙሪያው በቀለማት ደምቆ ከመሐሉ ጉልህ ቃል ሰፍሮበታል። መልዕክቱ የተጻፈው በእንግሊዝኛ ነው ‹‹ዲቮርስ›› ይላል። የጋብቻ ፍቺ እንደማለት።

ጉድ ፈላ። ‹‹ፍቺ›› ይሉት ቃል እኮ ትርጉሙ በጎ አይደለም። የትዳር፣ የጋብቻን መፍረስ የሚያረዳ ነው። ምን ያሻው ነው ጃል! እንዲህ አሽሞንሙኖ፣ አሳምሮ ‹‹እዩልኝ›› የሚለው? ነገሩ እያስደነቀኝ የሚያምረውን ትልቅ ኬክ በጥርጣሬ በዓይኔ ጫፍ ገረመምኩት። ልክ ነበርኩ። በጉልህ የተጻፈው ‹‹ዲቮርስ›› ይሉት ቃል መልሶ አፈጠጠብኝ።

አስገራሚው ጉዳይ ይህ ብቻ አይደለም። በኬኩ ዙሪያ በአማርኛ የተጻፈው መልዕክት በእጅጉ ያመራምራል። የጽሑፉን ሙሉ ሀሳብ በቀላሉ አምኖ ለመቀበል ይቸግራልና የአፍታ ጊዜን ልወስድ ግድ ነው። እንዲያም ሆኖ ጽሑፉን ከነትዝብቱ መቀበሌ አልቀረም። ‹‹ዲቮርስ›› ከሚለው ጽሑፍ በታች በአማርኛ የተጻፈውን ቃል አንድ በአንድ አነበብኩት። ‹‹እንኳንም ቀረብሽ፣ ቢቀር ዳቦ ድፊ፣ ጠላ ጥመቂ ነው›› ይላል።

ወዳጆቼ! እናንተም ይህን መሰል ጽሑፍ አይታችሁ፣ ታዝባችሁ ይሆናል። በእኔ በኩል ግን ግርምታው እስካሁን በውስጤ እንዳለ ነው። በአጭሩ የኬኩ ላይ መልዕክት የባልና ሚስቱ ፍቺ በመፅደቁ የሌሎች ሰዎችን የደስታ ስሜት ለማሳየት የተገለጸ ነው። ይህ መልዕክት ለብቻው ምንአልባት የሴቷን /የሚስቲቱን/ ባልንጀሮች ስሜት ያንጸበርቃል ባይ ነኝ።

መቼም አብዛኞቻችን ጊዜውን ማማረርና በጊዜው ማሳበብ ልምዳችን ሆኗል። ለዚህ አስገራሚ ጉዳይ ድንገት አስተያየት ብንጠየቅ ‹‹አይ! ጊዜ፣ ጊዜ አያሳየን፣ አያሰማን የለ›› እያልን ልናማርር እንችላለን። ለጊዜው በጊዜ ማሳበቡን እንተወውና ወዳነሳነው ሀሳብ እንመለስ።

እኔ አሁንም በሀሳብ በኬኩ ዙሪያ ነኝ። በዚህ ማኅበራዊ ገጽ ላይ የተለጠፈውን ጉደኛ ኬክ በዓይኔ ሕሊናዬ እየሳልኩ። የእናንተን አላውቅም እንጂ እኔ በኬኩ መቁረስ ጀርባ ይኖራሉ ያልኳቸውን እውነታዎች በምናብ እንዲህ እየገመትኩ ነው።

ፍቺ የፈጸመችው ወይዘሮ ይቅርታ፡- ወይዘሪት። ከፍርድ ቤት መልስ ለየት ባለ ልብስ ተውባ ከአናቷ ላይ የክብር አክሊል ደፍታ ትታየኛለች። በእርግጠኝነት እንደ እሷው ባለባበስ የደመቁ ሴቶች ዙሪያዋን ከበው ባለመደማመጥ ይንጫጫሉ። አብዛኞቹ የጥንዶቹን የቀደመ ታሪክ እያወሱ የሚሳሳቁ ናቸው። ጥቂቶቹ በባልንጀራቸው ትዳር መፍረስ አምነው ይሁንታው ላይ የሚያወጉ ይመስላል።

የኬኩ ዙሪያ ታዳሚዎች ፊት ላይ ጸጸት ይሉት አይነበብም። ሁሉም በተለየ ደስታና ፌሽታ እየቦረቁ የኬኩን መቆረስ ይናፍቃሉ። በእኔ ግምት በተጻፈው መልዕክት ላይ ተቃውሞ አቅራቢዎች እንደሌሉ ግልጽ ነው። በእያንዳንዱ ቃላት ላይ የስምምነት ሀሳባቸውን እንዳፀደቁ ይሰማኛል።

ምንአልባት የትዳሩ ‹‹እንኳን ቀረብሽ›› ኬክ የሚታጀበው በሻምፓኝና በሻማዎች ብቻ ላይሆን ይችላል። የፍቺው ደስታ ላሰባሰባቸው ታዳሚዎች የተዘጋጀ ምሳ፣ አልያም የራት ግብዣ አይጠፋም።

በእርግጠኝነት ይህ ዕቅድና ድርጊት በተለይ ከሴቷ ዘመድና ቤተሰቦች ይደገፍ አይመስለኝም። የትዳርን ክቡርነት የሚያውቁ፣ ልጃቸውን ለወግ ማዕረግ ያበቁ ወላጆች ለዚህ መሰሉ ዕቃ ዕቃ መሰል ጨዋታ እውቅናን አይሰጡም። እርግጥ ነው፣ በትዳር ዓለም ባልና ሚስት አይጋጩም፣ አይጣሉም ማለት አይደለም። ጠብ ጭቅጭቅና ምሬት በትክክል ይኖራል። ጎጆ ባለመስማማት ሲፈተን ግን ለመፍትሔው የራሱ ወግና ሥርዓት አለው።

ትዳር መሐል ንፋስ በገባ፣ ቅያሜ በመጣ ጊዜ ‹‹አንተም ተው፣ አንቺም ተይ›› ብሎ የሚዳኝ ሽማግሌ አይጠፋም። ባልና ሚስቱን በእኩል አስቀምጦ የሚዳኝ አስታራቂ ደግሞ ባብዛኛው በለስ ይቀናዋል። ትዳር እንዳይፈርስ፣ ጎጆ እንዳይፈታ፣ ልጆች እንዳይበተኑ የሚደረገው ማስማማት ተስፋ ባስቀረጠ ጉዳይ ላይ ፍሬ ይዞ ዓመታትን ሊቀጥል ይችላል።

በትዳር መሐል የሚፈጠሩ ችግሮች በዚህ መልኩ ሲፈቱ ‹‹እሰዬው›› ነው። ይህ አልሆን ብሎ የታሰበው ካልተሳካ ግን ትዳሩን በስምምነት አፍርሶ፣ ፍቺውን በፍርድ ቤት አፅድቆ በሠላም መለያየቱ አዲስ አይደለም።

አንዳንዴ በስምምነት የሚቋጩ ፍቺዎች ውሎ አድሮ ቤተሰባዊነት ይፈጥራሉ። እንዲህ ሲሆን ትናንት በ‹‹አንተ ትብስ፣ እኔ›› የተጋመደው አብሮነት ዛሬን በእህት ወንድምነት ተጣምሮ ትርጉም ያለው ሕይወት ይሰጣል።

ትዳር ከነችግሩም ቢሆን ሲፈርስ ቅር ያሰኛል። በእርግጥ እንከንና ችግር የዋጠው ሕይወት በይሉኝታ ብቻ ይቀጥል ላይባል ይችላል። መታወቅ ያለበት ግን ባብዛኛው መፍትሔ የሌለው ችግር አለመኖሩን ነው። ውሎ አድሮ ደግሞ ሁኔታዎች ሊለወጡ ይችላሉ። ዕድሜ ለመልካሞቹ ሽማግሌዎች ይሁንና ከባዱን አቅልለው፣ ቋጠሮውን የሚፈቱ ልበ ቀና አስታራቂዎች ሞልተዋል።

እኛ እስከዛሬ የምናውቀው፣ በሌሎችና በራስ ጥረት ጎጆ እንዲቆም ጥረት መኖሩን ነው። እኛ የምናውቀው ትዳር እንዳይፈርስ፣ ቤተሰብ እንዳይበተን ትግል መደረጉን ነው። ይህ አልሆን ብሎ ፍቺ ቢፈጸም ደግሞ የሌሎች ፈንጠዝያና ደስታ ታይቶ አይታወቅም። ‹‹እሰይ እነ እንቶኔ ተፋቱ፣ ተለያዩ›› ብሎ ጭፈራና ዕልልታ የለም። ለዛውም በገሀድ።

ዘንድሮ ግን ነገር ሁሉ ተቀይሯል። ለፈረሰ ትዳርና ጎጆ ከማዘን፣ ከማሰብ ይልቅ ለፍቺው ገሐዳዊ ዕውቅና ይሰጥ ይዟል። ዕውቅናው እኮ በተገቢው አካል ተችሮ ቢሆን አይደንቅም። በጥንዶቹ ልቦና ብቻ ቢቀርም እሰዬው ነው። ፍቺው ኬክ ተቆርሶለት፣ ሻምፓኝ ተከፍቶለት፣ በአጀብ ደምቆና በይሁንታ ፀድቆ ደስታን መፍጠሩ ግን እንደኔ በእጅጉ አሳዛኝ ያስብላል። ለዛውም ‹‹ትዳሩ እንኳንም ቀረብሽ፣አበጀሽ›› እየተባለ።

እስካሁን ከባሕላችን ውጭ የሆኑና ለእኛነታችን የሚጠቅሙ በርካታ ልማዶችን ከነጮቹ ወስደናል። እንዲህ ማድረጋችን እስከዛሬ ለኖርንበት ሕይወታችን ሲጠቅመን መኖሩን መካድ አይቻልም። አይበጁንም ባልናቸው መጤ ባሕሎች ላይ ግን ዓይን አንስተን፣ እጅ መሰብሰባችን ቢጠቅመን እንጂ አልጎዳንም። ይህ አይነቱን ማኅበራዊ እሴት የሚቃረን ጉዳይን ደግሞ ፈጽሞ ልንላመደው የማይገባ ተግባር ነው። ይህ ጅማሬ አጉል ልማድን ያጋባል። የትዳር ክቡርነትን ያቀልላል።

እኔ በግሌ ፍቺን አስመልክቶ በሚሰጠው የዕልልታ ዕውቅና ላይ መስማማትን አልሻም። ትዳር ሲፈታ፣ ጎጆ ሲበተን ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ‹‹እሰይ፣ጎሽ›› አያሰኝም። ለዛውም የሴትነት ወጉን አጣጥሎ፣ የነበረን ሙያ አንቋሾ ‹‹ቢቀር ዳቦ፣ቢረሳ ጠላው›› እየተባለ። እስቲ ልቦና ይስጠን። አበቃሁ።

# ዓለም አቀፍ

## ከ56 ዓመታት በፊት በደረሰ የአውሮፕላን አደጋ ከሞቱት ሰዎች መካከል የአራቱ አስከሬን ተገኘ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በሕንድ የተከሰከሰው አውሮፕላን ውስጥ ከነበሩ ሰዎች የአራቱ አስከሬን ከ56 ዓመታት ከስምንት ወር በኋላ ተገኝቷል።

በአደጋው ወንድሙን ያጣው ቶማስ ቶማስ የታላቅ ወንድሙ ቶማስ ቼሪያን አስከሬን ከ56 ዓመታት በኋላ መገኘቱን ያሳወቀው የፓታናምቲታ ፖሊስ ጣቢያ ስልክ ነው።

የሕንድ አየር ኃይል አውሮፕላን በአውሮፓውያኑ 1968 ነው 102 ሰዎች አሳፍሮ በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ምክንያት ሂማሊያን ተራራ ላይ የተከሰከሰው። የበረራ ቁጥሩ አይኤኤፍ ኤኤን-12 አውሮፕላን ለዓመታት አድራሻው አይታወቅም ነበር። አውሮፕላኑ ከራዳር ጋር ያለውን ግንኙነት የተቋረጠው በተራራማው ሮታንግ የተባለ ሥፍራ ነው።

በ2003 ተራራ የሚወጡ ሰዎች ከሚኞች መካከል የአንዱን አስከሬን ማግኘታቸው ትልቅ ዜና ሆኖ ነበር። ከዚህ በኋላ ለዓመታት የአደጋ ጊዜ ሠራተኞች እና ወታደሮች ፍለጋቸውን አጠናክረው እስከ 2019 ድረስም 8 ተጨማሪ አስከሬኖች ማግኘት ችለዋል። አልፎም የአውሮፕላኑ ስብርባሪ ተራራ ላይ ሊገኝ ችሏል።

ከቀናት በፊት ደግሞ በ1968 በተከሰከሰው አውሮፕላን ምክንያት የሞቱ አራት ሰዎች መገኘታቸው ተዘገበ። ከአራቱ አንዱ ቶማስ ቼሪያን ነው። "ለ56 ዓመታት ሲያስጨንቀን የነበረው ጉዳይ ድንገት መልስ አገኘ" ሲል ታናሽ ወንድሙ ቶማስ ለቢቢሲ ተናግሯል።

የጦር ኃይል ቴክኒሺያን የነበረው ቼሪያን ቤተሰቡ ካሉት አምስት ልጆች ሁለተኛው ሲሆን፣ አውሮፕላኑ ሲከሰከስ የ22 ዓመት ወጣት ነበር። በተሰጠው ግዳጅ መሠረት ሌህ ወደተባለችው የሂማሊያን ግዛት ሲያቀና ነው አደጋው የተከሰተው።

በአውሮፓውያኑ 2003 ከሚኞቹ መካከል የመጀመሪያው አስከሬን ሲገኝ ነው መሞቱ በይፋ የታወጀው። "አባታችን በ1990 ነው የሞተው፤ እናታችን ደግሞ በ1998። ሁለቱም የልጃቸውን የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ ዜና መስማት በጣም ይፈልጉ ነበር" ይላል ቶማስ። በጠቅላላው እስካሁን 13 አስከሬኖች ብቻ ናቸው የተገኙት።

ተራራማው ሥፍራ የአየር ሁኔታው ከባድ መሆኑ እና ብዙውን ጊዜ በበረዶ መሸፈኑ የአደጋ ጊዜ ሠራተኞችን ፍለጋ አዳጋች አድርጎታል። የቼሪያንን ጨምሮ የአራት ሰዎች አስከሬን የተገኘው ከባሕር ጠለል 16 ሺህ ጫማ ከፍታ ላይ በምትገኘው ዳካ ተራራ ላይ ነው። አስከሬኖቹን ያገኙት የሕንድ ጦር ሠራዊት አባላት እና የቲራንጋ የተራራ ላይ አደጋ ጊዜ ሠራተኞች ናቸው።

የፍለጋ ሠራተኞቹ የሳተላይት ምሥል፣ ራዳር እና ድሮኖችን ተጠቅመው አስከሬኖቹን ሊያገኙ እንደቻሉ የሕንድ ጦር ሠራዊት አባል የሆኑት ኮሎኔል ላሊት ፓላሪያ ተናግረዋል።

ቼሪያን የለበሰው የጦር ሠራዊት ዩኒፎርም 'ቶማስ ሲ' የሚል ፅሑፍ ነበረበት። ሲ የምትለው ስትገኝ ሌሎች ኪሱ ውስጥ የነበሩ መታወቂያ ካርዶች ማንነቱን ለመለየት አስችለዋል።

የቶማስ ቼሪያን ቤተሰቦች ምንም እንኳ በሞቱ ምክንያት ኀዘናቸው ጥልቅ ቢሆንም፤ በስተመጨረሻ አስከሬኑ መገኘቱ ግን ትልቅ እፎይታ እንደሆነ ይናገራሉ።

ባለሥልጣናት የቼሪያን አስከሬን በሕንድ ባንዲራ በተሸፈነ ሳጥን ለቤተሰቡ ያስረከቡ ሲሆን፣ የቀርብ ሥነ-ሥርዓቱ ኤላንቱር በምትባል ሥፍራ ካለ አንድ ቤተ-እምነት ተካሂዷል።

የቼሪያን ብቻ ሳይሆን የሌሎች ሟቾች ቤተሰቦችም ሐዘናቸውን እየተወጡ ይገኛሉ። በርካታ ሰዎች በአደጋው ምክንያት የሞቱ ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ዜና እየጠበቁ አርጅተዋል፤ ሞተዋል።

በቅርቡ አስከሬናቸው ከተገኙ መካከል ናራያን ሲንግ ነው። ሚስቱ ባሳንቲ ዴቪ የባሏን ዜና በጉጉት እየጠበቀች ሳለ ነው በ2011 ሞት የወሰዳት።

## ካማላ ሃሪስ የሕክምና ማስረጃቸውን ይፋ አደረጉ

በጋዜጣው ሪፖርተር



ዕጩ ፕሬዚዳንት ካማላ ሃሪስ ጤናቸው "በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ" ለመራጮች ለማረጋገጥ የሕክምና ማስረጃዎቻቸውን ይፋ ሲያደርጉ፤ ተፎካካሪያቸውን ዶናልድ ትራምፕም ተመሳሳዩን እንዲያደርጉ ግፊት እየበረታባቸው ነው።

የዲሞክራቲክ ፓርቲ ዕጩዋ ምክትል ፕሬዚዳንት ሃሪስ ተፎካካሪያቸው ዶናልድ ትራምፕ የሕክምና ማስረጃዎቻቸውን ይፋ ባለማድረጋቸው "ግልጽነት ይጎድላቸዋል" ሲሉ ከሰዋቸዋል።

ምክትል ፕሬዚዳንት ሃሪስ አክለውም የሪፐብሊካን ፓርቲው ዕጪ የቀድሞው ፕሬዚዳንት ትራምፕ "ለፕሬዚዳንትነት ብቁ ይሁኑ አይሁኑ የአሜሪካ ሕዝብ እንዲያውቅ አይፈልጉም" ብለዋል።

ነገር ግን የትራምፕ ረዳቶች የሕክምና መዛግብቶቻቸውን ይፋ ሳያደርጉ የግል ዶክተራቸው ጤናቸው "ያለምንም እክል በጥሩ ሁኔታ ላይ" እንደሚገኝ በመጥቀስ ምላሽ ሰጥተዋል።

የትራምፕ የምርጫ ቅስቀሳ ቡድን አባላት ዕጩው ፕሬዚዳንት "በጣሙን የተጨናነቀ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻን በብቃት እያካሄዱ" መሆናቸውን በመግለጽ፤ ሃሪስ የዚያን ያህል "ጥንካሬን የሚጠይቅ ብቃት የላቸውም" ሲሉ ተችተዋል።

በሁለቱ ፕሬዚዳንታዊ ዕጩዎች መካከል የትችት ቃላት ልውውጥ የተጀመረው የምክትል ፕሬዚዳንቷ ጽህፈት ቤት ካማላ ሃሪስ ፕሬዚዳንት ሆነው አሜሪካንን ለማገልገል የሚያስፈልገው "አካላዊ እና አእምሯዊ ጥንካሬ" እንዳለቸው ያሳያል ያሉትን የሕክምና ምርመራ ውጤት ይፋ ካደረጉ በኋላ ነው።

ለሦስት ዓመታት የሃሪስ ሐኪም ሆነው እያገለገሉ ያሉት የአሜሪካ ሠራዊት ኮሎኔል ዶ/ር ጆሽዋ ሳይመንስ በሕክምና ማስረጃው ላይ ምክትል ፕሬዚዳንቷ የተለያዩ ምርመራዎችን በማድግ ጤናማ እና ንቁ የሕይወት ዘይቤ እንዳላቸው አረጋግጠዋል።

የሃሪስ የሕክምና ውጤት ይፋ መደረጉን ተከትሎ የምርጫ ዘመቻ ቃል አቀባያቸው በማኅበራዊ ሚዲያ ገጻቸው ላይ "ዶናልድ ትራምፕ፤ አሁን የእርሶ ተራ ነው" ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

ዲሞክራቶች፤ ሪፐብሊካኖችን በመወከል የፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ተፎካካሪያቸው የሆኑት የ 78 ዓመቱን ትራምፕ በዕድሜ መግፋት እና በአእምሮ ብቃታቸው ሲተቿቸው ቆይተዋል።

ዶናልድ ትራምፕ በዚህ ወር መጨረሻ ላይ በሚካሄደው ምርጫ ለሁለተኛ ጊዜ ለፕሬዚዳንትነት የሚያሸንፉ ከሆነ ከአራት ዓመት በኋላ የመሪነት ዘመናቸውን ሲያጠናቅቁ፣ በመጪው ጥር ሥልጣን ከሚያስረክቡት ጆ ባይደን ጋር በአሜሪካ ታሪክ በዕድሜ የገፉ የአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት ታሪክን ይጋራሉ።

ከተቀናቃኞቻቸው በኩል የሕክምና ማስረጃዎቻቸውን ይፋ እንዲያደርጉ ግፊት የበረታባቸው ትራምፕ የምርጫ ዘመቻ ኃላፊ በሰጡት ምላሽ፣ የቀድሞው ፕሬዚዳንት የግል ዶክተራቸው እና በግድያ ሙከራ ከተካሄደባቸው በኋላ ሕክምና ያደረጉላቸው ሐኪሞች የጤንነታቸው ሁኔታ ተገልጿል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

"የሁለቱም ሐኪሞች ውጤት ዶናልድ ትራምፕ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት እና የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ ለመሆን በሚያስችል እጅግ በጣም ጥሩ በሚባል የጤና ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ደምድመዋል" ሲሉ ቃል አቀባዩ ተናግረዋል።

በጥቅምት ወር መጨረሻ ላይ በሚካሄደው የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ላይ የቀድሞው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ እና የወቅቱ ምክትል ፕሬዚዳንት ካማላ ሃሪስ በዕጩነት ቀርበዋል።

እስካሁን ያለውን የመራጮች ፍላጎትን በተመለከተ የተደረጉ ሀገር አቀፍ የሕዝብ አስተያየት መለኪያዎች ሃሪስ በጠባብ ነጥብ ትራምፕን እየመሩ መሆናቸውን ሲያመለክቱ፣ ከባድ ፉክክር በሚደረግባቸው ግዛቶች ውስጥ ሁለቱ ዕጩዎች በጣም ተቀራራቢ ውጤት አግኝተዋል።

# ስፖርት



# የኢትዮጵያ ክለቦች የአፍሪካ የእጅ ኳስ ሻምፒዮና ተሳትፎ

ብርሃን ፈይሳ

የአፍሪካ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን ከሚያካሂዳቸው ዓመታዊ ውድድሮች መካከል አንዱ የክለቦች ሻምፒዮና ነው። እአአ ከ1979 አንስቶ በመካሄድ ላይ የሚገኘው ይህ ሻምፒዮና ዘንድሮ ለ45ኛ ጊዜ በሞሮኮ ላዩን ከተማ አስተናጋጅነት መካሄድ ከጀመረ ቀናትን አስቆጥሯል። በአሕጉሪቱ በሚገኙ የእጅ ኳስ ሊጎች የተሻሉ ክለቦች በሚሳተፉበት በዚህ ሻምፒዮና አሸናፊው ክለብ ከሁሉም ኮንፌዴሬሽኖች የተወጣጡ ክለቦች በሚፋለሙበት ሱፐር ግሎብ ውድድር ላይ ተካፋይ ይሆናል።

ጠንካራ ፉክክርና አዝናኝ ውድድር በሚስተናገድበት በዚህ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ክለቦቿን ማሳተፍ ችላለች። ከትላንት በስቲያ በተጀመረው ውድድር 16 የወንድ እና 11 የሴት ክለቦች በመካፈል ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ከአዘጋጇ ሃገር ሞሮኮ እኩል ሦስት ክለቦችን በማሳተፍ በቀዳሚነት ልትቀመጥ ችላለች። ጥሩ ልምድ ሊገኝበት እንደሚችል በሚጠበቀው በዚህ መድረክ ላይ ሃገራቸውን የወከሉት ክለቦችም መቻል የእጅ ኳስ ክለብ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ የእጅ ኳስ ክለብ እና መቐለ 70 እንደርታ የእጅ ኳስ ክለብ መሆናቸውን ከኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን የተገኘው መረጃ ያመላክታል። ግብፅ፣ ኮንጎ፣ ካሜሩን እና ቤኒን ሁለት ሁለት ክለቦቻቸው በውድድሩ ሲካፈሉ ከኮትዲቯር እና ሴኔጋል አንድ አንድ ክለቦች የዋንጫ ፍልሚያውን ያደርጋሉ።

በወንድ ክለቦች መካከል የሚደረገው ውድድር በአራት ምድብ ሲከፈል፤ ጠንካራ ፉክክር ይጠበቃል። በተለይም ከመድረኩ ከፍተኛ ልምድ ማግኘት የቻሉትና በስፖርቱም ብቃታቸውን ያስመሰከሩት የግብፅና የአሕጉሪቷ ኃያላን ክለብ የሆኑት አል አህሊ እና ዛማሊክ እርስ በእርስ የሚያደርጉት የሻምፒዮናነት ፉክክር ተጠባቂ ነው። አል አህሊ በዚህ ውድድር ለስድስት ጊዜያት ሻምፒዮን ሲሆን፤ እጅግ ስኬታማው ዛማሊክ ደግሞ 12 ዋንጫዎችን በማንሳት የውድድሩ ድምቀቶች ናቸው። በወጣው ድልድል መሠረትም በምድብ አንድ የኢትዮጵያው መቐለ70 እንደርታ ከግብፁ አል አህሊ፣ ከኮንጎው ኢትአይሌ እንዲሁም ከኮንጎው ሲኤፍጄኤሶ ጋር ይገናኛል።

በዚህ መድረክ ለአራተኛ ጊዜ በመካፈል ከሌሎች ክለቦች የተሻለ ልምድ ያለው ቂርቆስ ክፍለ ከተማ የእጅ ኳስ ክለብ ከግብፁ ዛማሊክ፣ ከሞሮኮው ማውንታዳ እንዲሁም ከካሜሮኑ ፍሬንድሺፕ ክለቦች ጋር በምድብ ሦስት ተደልድሏል። ምድብ አራት ላይ የሚገኘው መቻል እጅ ኳስ ክለብ ደግሞ ከቤኒኑ አድጂድጃ፣ ከሞሮኮው ዊዳድ እንዲሁም ከሴኔጋሉ አስፋ ጋር ይገናኛል።

ኢትዮጵያ በ1970ዎቹ ጠንካራና ተፎካካሪ የእጅ ኳስ ቡድኖች የነበራት ቢሆንም ባለፉት በርካታ ዓመታት ስፖርቱ እየተዳከመ መጥተል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ስፖርቱ ዳግም እንዲያንሠራራና በአሕጉር ደረጃም ተወዳዳሪ ወደመሆን እየተመለሰ ይገኛል። ለዚህም ማሳያ የሚሆነው በቅርቡ በኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር መስፈርት መሠረት ከ69 ከመቶ በላይ በማሟላት በአንደኛ ደረጃ ላይ መቀመጡ ነው። ምሥራቅ አፍሪካ እጅ ኳስ ማኅበርን በአመራርነት ማገልገል እንዲሁም የዞን እና አሕጉር አቀፍ ውድድሮች በኢትዮጵያ እንዲካሄድ ማድረጉም ለዚህ ከፍተኛ ሚና ነበረው። የኢትዮጵያ እና የምሥራቅ የእጅ ኳስ ፕሬዚዳንት ፍትሕ




ወልደሰንበት(ዶ/ር) ኢትዮጵያ በዚህ ውድድር ሦስት ክለቦችን ስታሳትፍ በእጅ ኳስ ስፖርት ታሪክ ይህ የመጀመሪያው መሆኑን ይጠቁማሉ።

ከወራት በፊት በኢትዮጵያ አዘጋጅነት በተካሄደው እና 10 ሀገራት በተሳተፉበት የምሥራቅ አፍሪካ የዞን 5 ውድድር ላይ ከ18 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድኗ ሻምፒዮን በመሆን ለአሕጉር አቀፉ ውድድር ማለፉ የሚታወስ ነው። ይህ የአፍሪካ ሻምፒዮና ከጥቅምት 23 እስከ 27/2017 ዓ.ም በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት በአዲስ አበባ የሚካሄድ ይሆናል። ለዚህ ውድድርም ብሔራዊ ቡድኑ አሠልጣኞች የተመደቡለት ሲሆን፤ ክለባቸውን በመወከል በሞሮኮው ሻምፒዮና በመሳተፍ ላይ የሚገኙት ተጫዋቾች መመለስን ተከትሎ በቅርቡ ወደ 20 የሚጠጉ ወጣቶችን በመያዝ ዝግጅቱን እንደሚጀምርም ታውቋል።